# ምዕራፍ ፲

፩፤ ወሶበ ሰምአ አዶኒቤዜቅ ንጉሠ ኢየሩሳሌም ከመ ነሥአ ኢያሱ ለጋይ ወአጥፍኣ በከመ ገብረ ለኢያሪኮ ወለንጉሣ ፤

የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒቤዜቅ ኢያሱ ኢያሪኮንም እንዳጠፋት ንጉሧንም እንዳጠፋው ጋይን አጥፍቶ እጅ እንዳደረጋት በሰማ ጊዜ ፤

ወከመ ለሊሆሙ ሖሩ ሰብአ ገባዖን ኀበ ኢያሱ ወኀበ እስራኤል ወገረሩ ሎሙ ወነበሩ ማዕከሎሙ ፤

የገባዖን ሰዎችም ያጠፋናል ብለው ፈርተው ወደ ኢያሱና ወደ እስራኤል በፈቃዳቸው ሒደው እንደተገዙ በመካከላቸውም እንደኖሩ በሰማ ጊዜ ፤

፪፤ ፈርሀ እምኔሆሙ ጥቀ እስመ የአምር ከመ ዓባይ ሀገር ይእቲ ጥቀ ገባዖን በከመ አሐቲ እም አህጉረ መንግሥት እስመ ይእቲ ተዓቢ እምጋይ ወጽኑዓን እሙንቱ ኵሎሙ ዕደዊሃ ፤

ገባዖን ከሚገዛቸው አገሮች እንዳንዲቱ አገር እጅግ ታላቅ አገር እንደነበረች ያውቃልና፣ ከጋይም ትበልጥ ነበርና ፤ ሰዎቿም ሁሉ አርበኞች ነበሩና ከነሱም የተነሣ ፈጽሞ ፈራ ፤

፫፤ ወለአከ አዶኒቤዜቅ ንጉሠ ኢየሩሳሌም ኀበ ኤሌም ንጉሠ ኬብሮን ወኀበ ፊዶን ንጉሠ ኢያሪሞት ወኀበ ዮፍታሔ ንጉሠ ለኪሶን ወኀበ ዳቤር ንጉሠ አዶላም ፤

የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒቤዜቅም ወደ ኬብሮን ንጉሥ ወደ ኤሌምና ወደ ኢያሪሞት ንጉሥ ወደ ፊዶን፣ ወደለኪሶን ንጉሥ ወደ ዮፍታሔና ወደ አዶላም ንጉሥ ወደ ዳቤር ላከ ፤

፬፤ ወይቤሎሙ ንዑ ኀቤየ ወርዱ ኡኒ ከመ ንጽብኦሙ ለገባዖን እስለ ገብኡ ለሊሆሙ ኀበ ኢያሱ ወኀበ ደቂቀ እስራኤል ፤

ወደ ኢያሱና ወደ እስራኤል ልጆች በፈቃዳቸው የገቡ የገባዖንን ሰዎች እንወጋቸው ዘንድ መጥታችሁ እርዱኝ ብሎ ላከባቸው ፤

፭፤ ወተጋብኡ ወዐርጉ እሙንቱ ፭ቱ ነገሥተ አሞሬዎን ንጉሠ ኢየሩሳሌም ወንጉሠ ኬብሮን ወንጉሠ ኢያሪሞት ወንጉሠ ለኪሶን ወንጉሠ አዶላም ወበጽሑ እሙንቱኒ ወኵሎሙ ሕዘቢሆሙ ወአገትዋ ለገባዖን ወቀተልዋ ፤

የኢየሩሳሌም ንጉሥና የኬብሮን ንጉሥ ፤ የኢያሪሞት ንጉሥና የለኪሶን ንጉሥ ፤ የአዶላምም ንጉሥ እኒህ አምስቱ የአሕዛብ ነገሥታት ተሰብስበው ዘመቱ ፤

እነሱም ሠራዊቶቻቸውም ሁሉ ወደ ገባዖን ደርሰው ገባዖንን ከበው ወጓት ፤

፮፡ ወለአኩ ሰብአ ገባዖን ኀበ ኢያሱ ውኅበ ትዕይንተ እስራኤል ውስተ ገልገላ ፤

የገባዖን ሰዎችም ከኢያሱና ከእስራኤል ወገኖች ዘንድ ወደገልገላ መልእክተኛ ላኩ ፤

ወይቤሉ ኢትትህከይ እዴከ በእንተ አግብርቲከ ዕርግ ኀቤነ ወፍጡነ ርድአነ ወአድኅነነ እስመ ተጋብኡ ላዕሌነ ኵሎሙ ነገሥተ አሞሬዎን እለ ይነብሩ ውስተ አድባር ፤

በደጋ የሚኖሩ የአሞሬዎን ነገሥታት ሁሉ በኛ ላይ ተሰብስበው ዘምተዋልና ስለኛ ስለባሮችህ ሥልጣንህ ቸል አትበል ፤ ወደኛ መጥተህ ፈጥነህ ርዳን አድነን ብለው ላኩ ፤ አንድም ስለኛ ስለባሮችህ እጅህ ከመወርወር ፤ ቃልህ ከመምከር ቸል አትበል ብለው ላኩ ፤

፯፡ ወዐርገ ኢያሱ እምገልገላ ውእቱ ወኵሉ ሕዝብ መስተቃትላን ምስሌሁ ወኵሉ ጽኑዕ ኃይሉ ፤

ኢያሱም ይህን ሰምቶ ከአርበኞች ወገኖቹ ጋር ኃይል ያላቸውን ሰዎች ሁሉ አስከትሎ ከገልገላ ወደ ገባዖን ዘመተ ፤

፰፡ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ኢትፍርሆሙ እስመ ውስተ እዴከ አግብኦሙ ወአልቦ ዘይተርፍ እምኔሆሙ ቅድሜከሙ ወኢ፩ዱ ፤

እግዚአብሔርም ኢያሱን እንዲህ አለው፤ እነዚህን ሁሉ በጅህ እጥላቸዋለሁና ከነሱ አንድ ሰው እንኳ የሚቀር የለምና አትፍራቸው አለው ፤

፱፡ ወበጽሖሙ ኢያሱ ግብተ በሌሊት ወዓአ እምገልገላ ፤

ኢያሱም ከገልገላ ወጥቶ ሲገሰግስ አድሮ ድንገት በሌሊት ደረሰባቸው (አደጋ ጣለባቸው)፤

፲፡ ወአደንገፆሙ እግዚአብሔር እምቅድመ ገጾሙ ለእስራኤል ወቀጥቀጦሙ ዓቢየ ቅጥቃጤ በገባዖን ወጐዩ ውስተ ፍኖተ ምዕራገ ቤቶሮን ወዴገንዎሙ እስከ አዜቃ ወእስከ መቄዳ ፤

እግዚአብሔር አሕዛብን ከእስራኤል ፊት መገለጽ የተነሣ አስደነገጣቸው ፤ በጽኑ ጥፋትም አጠፋቸው፤ ወደ ቤቶሮን አቀበት ጐዳና ሸሹ ፤ እስራኤል ተከትለው እስከ አዜቃና እስከ መቄዳ ድረስ ወጓቸው ፤

፲፩፡ ወሶበ ነትኡ እምቅድመ ገጾሙ ለደቂቀ እስራኤል በውስተሙራዳቲሁ ለቤቶሮን ወወገሮሙ እግዚአብሔር እምሰማይ በዕብነ በረድ እስከ አዜቃ ፤

ከእስራኤል ፊት ድል ተነሥተው ወደ ቤቶሮን ቍልቍለት

በሸሹ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰማይ የድንጋይ በረዶ አውርዶ እስከ አዜቃ ድረስ አጠፋቸው ፤

ወፈድፈዱ እለ ሞቱ በዕብነ በረድ እምእለ ቀተሉ ደቂቀ እስራኤል በሐፂኖሙ በውስተ ቀትል ፤

የእስራኤል ልጆች ከሰልፍ በጦር ከገደሏቸው ይልቅ በድንጊያ በረዶ የሞቱት በዙ ፤

፲፪፤ ወይእተ አሚረ ተናገረ ኢያሱ ምስለ እግዚአብሔር አመ እግብኦሙ እግዚአብሔር ለአሞሬዎን ውስተ እዴሆሙ ለደቂቀ እስራኤል ወይቤ ኢያሱ ለትቁም ፀሐይ መንገለ ገባዖን ወወርኅኒ መንገለ ቈላተ ኤሎም ፤

እግዚአብሔር የአሞሬዎንን ነገሥታት በእስራኤል ልጆች እጅ በጣላቸው ጊዜ ኢያሱ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገረ ማለት ፀሐይ በገባዖን ፤ ጨረቃ በኤሎም ቈላ ትቁም ብሎ እግዚአብሔርን ለመነ ፤

፲፫፤ ወቆሙ ፀሐይ ወወርኅ በበምቅዋሞሙ በኀበ ሀለዉ እስከ አጥፍኦሙ እግዚአብሔር ለፀሮሙ ፤

እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እስኪያጠፋቸው ድረስ ፀሐይና ጨረቃ በያሉበት ቆሙ ፤

ወናሁ ተጽሕፈ ዝንቱ ውስተ ዝንቱ መጽሐፍ በጊዜሃ ወቆመት ፀሐይ ማዕከለ ሰማይ ወኢሖረት መንገለ ምዕራብ አምጣነ አሐቲ ዕለት ፍጽምት ፤

ይህ ነገር እነሆ ያንጊዜ በዚህ መጽሐፍ ተጻፈ ፤ ፀሐይም በሰማይ መካከል ቆመች አንድ ቀን ያህል ፈጽሞ ወደ መግቢያዋ አልሔደችም ፤

፲፬፤ ወኢኮነት ከመ ይእቲ ዕለት ኢ እምቅድሜሃ ወኢ እምድኅሬሃ ከመ ያውሥአ እግዚአብሔር ለቃለ እጓለ እመሕያው ወእግዚአብሔር ጸብአ ሎሙ ለእስራኤል ፤

እግዚአብሔር የሰውን ጸሎቱን ይሰማው ዘንድ ከዚያ አስቀድሞም ቢሆን ከዚያ በኋላም ቢሆን እንደዚህ የተደረገበት ቀን የለም ፤ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ጠላቶቻቸውን አጠፋላቸው ፤

፲፭፤ ወገብኡ ዳግመ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ ውስተ ገልገላ ትዕይንቶሙ ፤

ዳግመኛ ኢያሱና እስራኤል ሁሉ ወደከተማቸው ወደገልገላ ተመለሱ ፤

፲፮፤ ወጐዩ እልክቱ ፭ቱ ነገሥት ወተኀብኡ ውስተ በአት ዘመቄዳ ፤

እነዚህ አምስቱ ነገሥታት ሸሽተው በመቄዳ ባለው ዋሻ ተሠወሩ መቃብራችን ነው ሲሉ ፤

፲፯፤ ወዜነውዎ ለኢያሱ ወይቤልዎ ተረክቡ እልክቱ ፭ቱ ነገሥት ውስተ በአተ መቄዳ ኅበ ተኃብኡ ።

እኒህ ፭ቱ ነገሥታት ተሠውረው በተሰበሰቡበት በመቄዳ ዋሻ ተገኙ ብለው ለኢያሱ ነገሩት ፤

፲፰፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ አንኰር ኰሩ ዕብነ ውስተ አፉሃ ለይእቲ በአት ወአንብሩ ዕደወ ላዕሌሆሙ እለ የዐቅብዎሙ ።

ኢያሱም ታላቅ ድንጋይ አገላብጣችሁ የተሠወሩባትን ዋሻ ግጠሟት የሚጠብቋቸውም ሰዎች አኑሩባቸው አላቸው ፤

፲፱፤ ወአንትሙሰ ኢትቁሙ ዴግኑ ፀሬሆሙ ኵሎ እስከ ጽንፎሙ ወኢታብኅዎሙ ይባኡ ውስተ አህጉሪሆሙ እስመ አግብኦሙ እግዚአብሔር አምላክነ ውስተ እዴነ ።

እናንተ ግን አትቁሙ ጠላቶቻችሁንም ሁሉ እስከ ዳርቻቸው ድረስ ተከተሏቸው (እየተከተላችሁ አጥፏቸው) ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በጃችን ጥሏቸዋልና በጤና ወደ ሀገራቸው ይገቡ ዘንድ አታሰናብቷቸው አላቸው ፤

፳፤ ወእምዝ ሶበ አኅለቁ ቀቲሎቶሙ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ቀትለ ዓቢየ ጥቀ ዘአልቦ ማኅለቅት ወእለሂ ድኅኑ እምኔሆሙ ውስተ አህጉር ጽኑዓት ።

ከዚህ በኋላ ኢያሱና እስራኤል ለጥፋቱ ፍጻሜ የሌለው ጽኑ ሰልፍ አድርገው ባጠፏቸው ጊዜ ከነዚያ የዳኑትም ወደዳኑ አገሮች በገቡ ጊዜ ፤

፳፩፤ ወገብኡ ኵሉ ሕዝብ ውስተ ትዕይንት ኅበ ኢያሱ ውስተ መቄዳ ድኑናኒሆሙ ወአልቦ ዘለሐሶሙ በልሳኑ መኑሂ ለደቂቀ እስራኤል ።

ሕዝቡ ሁሉ ኢያሱ ወዳለበት ወደ መቄዳ በደኅና ተመለሱ በእስራኤል ልጆች ላይ ማንም ማን ጥቂት ስንኳ መከራ ያመጣባቸው የለም ፤

፳፪፤ ወይቤሎሙ አርኅውዋ ለዛቲ በአት ወአምጽእዎሙ ኀቤየ ለእልክቱ ፭ቱ ነገሥት እምዛቲ በአት ።

ኢያሱም ያችን ዋሻ ክፈታችሁ እነዚያን ፭ቱን ነገሥታት ከዚያች ዋሻ አውጥታችሁ ወደኔ አምጧቸው አላቸው ፤

፳፫፤ ወገብሩ ከማሁ ወአውፅእዎሙ ለእልክቱ ፭ቱ ነገሥት እምውስተ ይእቲ በአት ለንጉሠ ኢየሩሳሌም ወለንጉሠ ኬብሮን ወለንጉሠ ኢያሪሞት ወለንጉሠ ለኪሶን ወለንጉሠ አዶላም ወወሰድዎሙ ኀበ ኢያሱ ።

እንዳዘዛቸውም አደረጉ ፤ የኬብሮንን ንጉሥና የኢየሩሳሌምን ንጉሥ ፤ የለኪሶንን ንጉሥና የኢያሪሞትን ንጉሥ ፤ የአዶላምንም

ንጉሥ እኒህን ፭ቱን ነገሥታት ከዚያች ዋሻ አውጥተው ወደ ኢያሱ ወሰዷቸው ፤

፳፬፤ ወጸውዖሙ ኢያሱ ለኵሉ እስ ራኤል እለ ተቃተሉ ወለእለ ሖሩ ምስሌሁ ወይቤሎሙ ደዩ እገሪሆሙ ላዕለ ክሣዳቲሆሙ ወወደዩ እገሪ ሆሙ ላዕለ ክሣዳቲሆሙ ።

ኢያሱም የተዋጉትንና ከርሱ ጋር ወደ ሰልፍ የሔዱትን እስ ራኤልን ሁሉ ጠርቶ እግር ካን ገት አድርጋችሁ እሠሯቸው አላቸው እነሱም እግር ካንገት አድርገው አሠሯቸው ፤ አን ድም ደዩ እገሪክሙ ላዕለ ክሣ ዳቲሆሙ ይላል ፣ በእግራችሁ እየረገጣችሁ ግደሏቸው አላ ቸው በእግራቸው እየረገጡ ገደሏቸው ፤

፳፭፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ኢትፍር ህዎሙ ወኢትደንግፁ እምኔሆሙ ትብዑ ወጽንዑ እስመ ከመዝ ይገ ብሮሙ እግዚአብሔር ለኵሎሙ ፀርክሙ እለ ትጸብእዎሙ አንትሙ ፣

ኢያሱም አትፍሯቸው ከነዚህም የተነሣ አትደንግጡ እናንተ የምትወጓቸው ጠላቶቻችሁን እግዚአብሔር እንዲህ ያደርጋ ቸዋልና በርቱ ጽኑ አላቸው ፤

፳፮፤ ወእምዝ ቀተልዎሙ ወረገዝ ዎሙ ወሰቀልዎሙ ላዕለ ፭ቱ ዕፀው ወነበሩ ስቁላኒሆሙ እስከ ሠርክ ፣

ከዚህ በኋላ በጦር ወግተው ገድለው ባምስት እንጨት ላይ ሰቀሏቸው እስከ ማታ ድረስ ተሰቅለው ዋሉ ፤

፳፯፤ ወእምዝ ሶበ ዓርበ ፀሐይ አዘዘ ኢያሱ ያውርድዎሙ ወአውረድዎሙ እምዕፀው ወገደፍዎሙ ውስተ ይእቲ በአት እንተ ውስቴታ ተነብዑ ወአ ንኰርኰሩ እብነ ዓቢየ ዲቤሃ ለይ እቲ በአት ፣

ፀሐይ በገባ ጊዜ ያወርዷቸው ዘንድ አዘዘ፣ ከየተሰቀሉበት እን ጨት አውርደው በተሸሸጉበት በዚያች ዋሻ ጣሏቸው ፣ ታላቅ ደንጊያም አገላብጠው ያችን ዋሻ ገጠሟት ፤

፳፰፤ ወለመቄዳሂ ነሥእዋ በይእቲ ዕለት ወለንጉሣ ቀተልዎ በአፈ ሐፂን ወአጥፍእዎሙ ለኵሉ ዘመ ንፈስ ዘውስቴታ ፣

በዚያች ቀንም መቄዳን እጅ አደረጓት፣ ንጉሧንም በጦር ገደ ሉት ፣ በውስጧ የወንድ አካል ያላቸውን ሁሉ አጠፏቸው ፤

ወኢያትረፉ ውስቴታ ነፋጺተ ወኢ መኑሂ አልቦ ዘድኅነ ወገብርዎ ለን ጉሠ መቄዳ በከመ ገብርዎ ለንጉሠ ኢያሪኮ ፣

በውስጧ የሸሸች ሴትንስ እንኳ አላስቀሩም፣ ማንም ማን የዳነ የለም ፣ የኢያሪኮን ንጉሥ እንዳ ጠፉት የመቄዳንም ንጉሥ እን ደዚያው አጠፉት ፤

፳፱፤ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራ
ኤል ምስሌሁ እመቄዳ ውስተ ልብና
ወተቃተላ ለልብና ፣

ኢያሱ ከእስራኤል ሁሉ ጋር
ከመቄዳ ወደ ልብና ሔደ ልብ
ናንም ወጋት ፤

፴፤ ወአግብኣ እግዚአብሔር ውስተ
እደሆሙ ለእስራኤል ወነሥእዋ
ወለንጉሣ ቀተሉ በአፈ ሐፂን ወኢ
ያትረፈ ውስቴታ እምኵሉ ዘመን
ፈስ ፣

እግዚአብሔር ልብናን በእስራ
ኤል እጅ ጣላት ፣ እጅም አደረ
ጓት ፣ ንጉሧንም በጦር ገደለው
በውስጧም የወንድ አካል ካለው
ሁሉ አላስቀረም ፤

ወኢያድኅነ ወኢአሐደ ነፍሴ እም
ኔሆሙ ወገብርዎ ለንጉሣ በከመ
ገብርዎ ለንጉሠ ኢያሪኮ ፣

ከነሱ አንድ ስንኳን ሸሽቶ ያመ
ለጠ የለም ፣ የኢያሪኮን ንጉሥ
እንዳጠፉት የልብናንም ንጉሥ
አጠፉት ፤

፴፩፤ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራ
ኤል ምስሌሁ እምልብና ውስተ
ለኪሶ ወነበሩ ላዕሌሃ ወተቃተልዋ ፣

ኢያሱም ሔደ ፣ ከእርሱ ጋራ
ያሉ እስራኤልም ሁሉ ከልብና
ወደ ለኪሶ ተጉዘው በላይዋ
ሁነው ሠፍረው ተዋጓት ፤

፴፪፤ ወአግብኣ እግዚአብሔር ለለ
ኪሶ ውስተ እደሆሙ ለእስራኤል
ወነሥእዋ በሳኒታ ዕለት ወቀተል
ዎሙ በአፈ ሐፂን ወአጥፍእዋ በከመ
ገብርዋ ለልብና ፣

እግዚአብሔር ለኪሶን በእስራ
ኤል እጅ ጣላት በማግስቱም
እጅ አደረጓት ፣ ሕዝቡንም
በጦር አጠፏቸው ፣ ልብናን እን
ዳጠፏት እሷንም አጠፏት ፤

፴፫፤ ወዐርገ ይእተ አሚረ ኤላም
ንጉሠ ጋዜስ ከመ ይርአያ ለለኪሶ
ወቀተሎ ኢያሱ በአፈ ሐፂን ወለሕ
ዝቡሂ እስከ ኢያትረፈ እምኔሆሙ
ነፋጺተ ወአልቦ ዘድኅነ ፣

ያን ጊዜ የጋዜስ ንጉሥ ኤላም
ለኪሶን ያያት ዘንድ ወጣ ፣
ኢያሱ ተቀብሎ በጦር ወግቶ
ገደለው ፣ ከነዚያ የምትሸሽ
ሴትን ስንኳን ሳያስቀር ወገኖ
ቹን ሁሉ ገደላቸው ፣ ከነሱም
የዳነ የለም ፤

፴፬፤ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል
ምስሌሁ እምለኪሶ ውስተ አዶላም
ወነበሩ ላዕሌሃ ወተቃተልዋ ፣

ኢያሱና እስራኤል ሁሉ ከለኪሶ
ወደ አዶላም ሒደው በላይዋ
ሠፍረው ተዋጓት ፤

፴፭፤ ወአግብኣ እግዚአብሔር ውስተ
እደሆሙ ለእስራኤል ወነሥእዋ
በይእቲ ዕለት ወቀተልዋ በአፈ
ሐፂን ወቀተሉ ኵሎ ዘመንፈስ
ዘውስቴታ በከመ ገብርዋ ለለኪሶ ፣

እግዚአብሔርም በእስራኤል
እጅ ጣላት ፣ በዚች ቀንም እጅ
አድርገው በጦር ወጓት፣ ለኪሶን

እንዳደረጓት (እንዳጠፏት) በው ስጧ ያለ የወንድ አካል ያለውን ሁሉ ገደሉ ፤

፴፮፥ ወሖረ ኢያሱ ወኵሉ እስራ ኤል ምስሌሁ እምአዶላም ውስተ ኬብሮን ወነበሩ ላዕሌሃ ወቀተልዋ በአፈ ሐፂን ወለኵሉ ዘመንፈስ ዘው ስቴታ ፤

ኢያሱና እስራኤል ሁሉ ከአዶ ላም ወደ ኬብሮን ተጉዘው በላ ይዋ ሠፍረው በጦር አጠፏት፣ በውስጧ የወንድ አካል ያለውን ሁሉ አጠፉ ፤

፴፯፥ ወአልቦ ዘድኅነ እምኵሉ ዘው ስቴታ ወአጥፍእዋ በከመ ገብርዋ ለአዶላም ፤

በውስጧ ካለው ሁሉ የዳነ የለም፣ አዶላምን እንዳጠፏት እሷንም አጠፏት ፤

፴፰፥ ወገብአ ኢያሱ ወኵሉ እስራ ኤል ውስተ ዳቤር ወነበሩ ላዕሌሃ ፤

ኢያሱ ከእስራኤል ሁሉ ጋር ወደ ዳቤር ተመልሶ በላይዋ ሠፍረው ተቀመጡ ፤

፴፱፥ ወነሥእዋ ወቀተልዎ ለንጉሣ በአፈ ሐፂን ወለአህጉሪሃኒ ወለኵሉ ዘመንፈስ ዘውስቴታ ፤

አገሪቱን እጅ አደረጓት፣ ንጉሧ ንም በጦር ወግተው ገደሉት ፤ አገሮቿንም አጠፏቸው ፤ በው ስጧ የወንድ አካል ያለውን ሁሉ አጠፉ ፤

ወአልቦ ዘአትረፈ ውስቴታ ዘድኅነ ወአጥፍእዋ በከመ ገብርዋ ለኬብሮን ወለንጉሣ ከማሁ ገብርዋ ለዳቤር ወለንጉሣ ፤

በውስጧ ያስቀሩት ከጥፋት የዳነ የለም፣ ኬብሮንን ከንጉሧ ጋር እንዳጠፏት ዳቤርንም ከን ጉሧ ጋር እልም ድርግም አድ ርገው አጠፏት ፤

፵፥ ወቀተለ ኢያሱ ኵሎ ምድሮሙ ለደወለ አድባር ወለናቤ ወለአንቃ ላቲሃ ወለአሴዶት ወነገሥቶሙ ፤

ኢያሱ የናቤዎንንና የደጋዎቹን አውራጃዎች አሴዶትንና አውራ ጃዎቿን ንጉሦቻቸውንም ሁሉ አጠፋ ፤

ወአልቦ ዘተርፈ እምኔሆሙ ወዘድ ኅነ ወኵሎ ዘመንፈሰ ሕይወት አጥ ፍአ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር አም ላከ እስራኤል ፤

ከነዚያ ከሞት የቀረ ከጥፋት የዳነ የለም፣ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር እንዳዘዘው በነ ፍስ ሕያው የሆነ ሰውን ሁሉ አጠፋ ፤

፵፩፥ ወቀተሎሙ ኢያሱ እምቃዴስ በርኔ እስከ ጋዛ ወኵሎ ጎሣም እስከ ገባዖን ፤

ኢያሱ ከቃዴስ በርኔ ጀምሮ እስከ ጋዛ ከጎሣም ጀምሮ እስከ ገባዖን አጠፋቸው ፤

፵፪፤ ወቀተለ ኢያሱ ኵሎ ነገሥቶሙ ወምድሮሙኒ አኀዘ በምዕር እስመ እግዚአብሔር ይጸብእ ሎሙ ለእስራኤል ፤

ኢያሱ የሕዝብን ነገሥታት ሁሉ አጥፍቶ አገራቸውን ባንድ ጊዜ ያዘ ፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል ቁሞ ጠላቶቻቸውን ያጠፋላቸው ነበርና ፤

፵፫፤ ወገብአ ኢያሱ ወኵሉ እስራኤል ምስሌሁ ኀበ ትዕይንት ውስተ ገልገላ ፤

ኢያሱ እስራኤልን ሁሉ አስከትሎ (ከእስራኤል ሁሉ ጋር) በገልገላ ወደአለው ሠፈራቸው ተመለሰ ።

## ምዕራፍ ፲፩

## ጉባኤ

፩፤ ወሰበ ሰምዐ ኢያቢስ ንጉሠ አሦር ለአከ ኀበ ኢዮባብ ንጉሠ አምሮን ወኀበ ንጉሠ ሲሞአን ወኀበ ንጉሠ አዜፍ ፤

የአሦር ንጉሥ ኢያቢስ የኢያሱን መምጣት በሰማ ጊዜ ወደ አምሮን ንጉሥ ወደ ኢዮባብና ወደ ሲሞአን ንጉሥ ወደ አዜፍ ንጉሥ ላከ ፤

፪፤ ውኀበ ነገሥት እለ መንገለ መስዕ እንተ ውስተ አድባር ወውስተ ዓረባ ዘአዜብ በቅድመ ኬኔሬት ወውስተ አሕቃላት ዘፊናዶር ፤

በመስዕ በኩል (በቀኝ በኩል) በደጋ አገር ወደሚኖሩና በኬኔሬት አንፃር በአዜብ በኩል ወደሚኖሩ ነገሥታት ወደ ፊናዶርም አውራጃ ላከ ፤

፫፤ ወውስተ ባሕር ዘከነዓን ዘመንገለ ጽባሕ ወውስተ ባሕር ዘአሞሬዎን ወኬዌዎን ወኢያቡሴዎን ወፌርዜዎን እለ ውስተ አድባር ወኬጤዎን እለ ውስተ አሕቃላት ወ[illegible]ብተ መሲውማን ፤

በከነዓን በምዕራብና በምሥራቅ ወዳሉ ወደ አሞሬዎንና ወደኬዌዎን በደጋ ወዳሉ ወደ ፌርዜዎንና ወደኢያቡሴዎን በሴውማንና በአውራጃዋ ወዳሉ ወደ ኬጤዎን ወደአሕዛብ ነገሥታት ላከ ፤

፬፤ ወወፅኡ እሙንቱ ወትዕይንቶሙኒ ምስሌሆሙ ከመ ኆፃ ባሕር ብዝኆሙ ወአፍራስ ወሠረገላት ብዙኃን ጥቀ ፤

የላከባቸው ነገሥታቱ ከሠራዊቶቻቸው ጋር ብዛታቸው እንደ ባሕር አሸዋ ሁነው ወጡ ሠረገላዎቻቸውና ፈረሶቻቸውም እጅግ ብዙዎች ነበሩ ፤

፭፤ ወተጋብኡ ኵሎሙ ነገሥት ወመጽኡ ኀቡረ ወተአንገዝዎሙ ይት

ቃተልዎሙ ለእስራኤል በኀበ ማየ
ማሮን ፣

ነገሥታቱ ሁሉ ተሰብስበው ባን
ድነት መጥተው እስራኤልን
በማሮን ውሃ ይወጓቸው ዘንድ
በጦርነት ተያያዟቸው ፤

፮፤ ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ
ኢትፍራህ እምቅድመ ገጾሙ እስመ
ጌሠመ በዛቲ ጊዜ አነ አገብአሙ
ከመ ይትቃተሉ በቅድመ እስራኤል
ወለአፍራሲሆሙኒ ምትር ሥረዊ
ሆሙ ወሠረገላቲሆሙኒ አውዒ
በእሳት ፣

እግዚአብሔር ኢያሱን በእስራ
ኤል ፊት ተዋግተው ይሞቱ
ዘንድ እኔ ነገ በዚች ጊዜ በጅህ
እጥላቸዋለሁ እና ከፊታቸው
የተነሣ አትፍራ ፣ የፈረሶቻቸ
ውን ቋንጃቸውን ቁረጥ፣ ሠረገ
ሎቻቸ ውንም በእሳት አቃጥል
አለው ፤

፯፤ ወሖሩ ኢያሱ ወኵሎሙ ሕዝብ
መስተቃትላን ላዕሌሆሙ ኀበ ማየ
ማሮን ወወረዱ ላዕሌሆሙ እምአድ
ባር ወአውገብዎሙ ፣

ኢያሱና አርበኞች የሚሆኑ
ሠራዊቱ ሁሉ ወደ ማሮን ወንዝ
ሔዱ ከተራራውም ወደነሱ
ወርደው (አደንገጽዎሙ ሲል
ነው) አሕዛብን አስፈሯቸው
አስደነገጧቸው ፤

፰፤ ወአግብአሙ እግዚአብሔር
ውስተ እዴሆሙ ለእስራኤል ወዴገ
ንዎሙ እንዘ ይቀትልዎሙ እስከ
ሲዶና ዓባይ ወእስከ ማሴሮን ወእ
ስከ አሕቃላተ ምሳህ ዘመንገለ ጽባ
ሒሁ ወቀተልዎሙ ወኢያትረፉ
እምኔሆሙ ነፋጺተ ፣

እግዚአብሔርም አሕዛብን በእ
ስራኤል እጅ ጣላቸው ፣ ደገኛ
ሀገር እስከምትሆን እስከ ሲዶ
ናና እስከ ማሴሮን ድረስ በምሥ
ራቅ በኩል እስካለ እስከ ምሳህ
አውራጃ ድረስ እየተከተሉ አጠ
ፏቸው ከነሱ ሸሽተኛ ስንኳን
አላስቀሩም ፤

፱፤ ወገብሮሙ ኢያሱ በከመ አዘዞ
እግዚአብሔር ወመተረ ሥረዊሆሙ
ለአፍራሲሆሙ ወሠረገላቲሆሙኒ
አውዓየ በእሳት ፣

ኢያሱም እግዚአብሔር አጥፋ
ቸው ብሎ እንዳዘዘው እልም
አድርጐ አጠፋቸው ፣ ፈረሶቻቸ
ውንም ቋንጃ ቋንጃቸውን እየ
ቆረጠ ጣላቸው ፣ ሠረገሎቻቸ
ውንም በእሳት አቃጠለ ፤

፲፤ ወተመይጠ ኢያሱ በእማንቱ
መዋዕል ወነሥአ ለአሦር ወለንጉሣ
ቀተሎ በሰይፍ እስመ አሦር ቀዲሙ
ርእሶሙ ይእቲ ለእሉ ኵሎሙ ነገ
ሥት ፣

ኢያሱም በዚያ ወራት ተመልሶ
አሦርን እጅ አደረጋት ፣ ንጉሧ
ንም በሰይፍ ገደለው ፣ አሦር
ከቀድሞ ጀምሮ የኒህ ሁሉ ነገ
ሥታት መዲና ነበረችና እጅ

አደረጋት ፤ አንድም አሦር የነገሥታቱ ሁሉ መዲና ናት ፤

፲፩፤ ወቀተሉ ኵሎ ዘነፍስ ዘውስቴታ በሐፂን ወአጥፍእዎሙ ለኵሎሙ እስከ ኢያትረፉ ውስቴታ ዘመንፈስ ወአውዓያ ለአሦር በእሳት ወለኵሉ አህጉረ እሉ ነገሥት ፤

በውስጧ የወንድ አካል ያለውን አንድስ እንኳ ሳያስቀሩ ሁሉን አጠፉ አሦርንም በእሳት አቃጠሳት፤ የሊህን ነገሥታት አገር ሁሉ በእሳት አቃጠለ ፤

፲፪፤ ወነሥአሙ ኢያሱ ለነገሥቶሙ ወቀተሎሙ በሐፂን ወሠረዎሙ በከመ አዘዞ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብሔር ፤

ኢያሱም ነገሥታቱን ይዞ የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ እንዳዘዘው በጦር ነቃቅሎ አጠፋቸው ፤

፲፫፤ ወባዕደሰ አህጉረ ኵሎ ዘአድያም ኢያውዓዩ እስራኤል እንበለ አሦር ባሕቲታ ዘአውዓዩ ፤

ነገር ግን እስራኤል ያቃጠሉ አሦርን ብቻ ነው እንጂ ከአሦር በቀር ባውራጃቸው ያለ ሌላውን አገር ሁሉ አላቃጠሉም ፤

፲፬፤ ወበርበሩ ደቂቀ እስራኤል ለርእሶሙ ኵሎ በርበሮ ወሎሙሰ ሠረውዎሙ እስከ አጥፍእዎሙ ለኵሎሙ በአፈ ሐፂን ወኢያትረፉ እምኔሆሙ ወኢ ፩ደ ዘመንፈስ ፤

የእስራኤል ልጆች ገንዘቡን ሁሉ ለራሳቸው ወረሩ ዘረፉ ፤ ሁሉንም በጦር እልም አድርገው እስኪያጠፏቸው ድረስ ደርሰው ከነሱ አንድ ሰውስ እንኳ አላስቀሩም ፤

፲፭፤ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ቍልዔሁ ወሙሴ አዘዞ ለኢያሱ ከማሁ ገብረ ኢያሱ ወኢኀደገ ምንተኒ እምኵሉ ዘአዘዞ ሙሴ ፤

እግዚአብሔር ለወዳጁ ለሙሴ እንዳዘዘው ሙሴም ኢያሱን እንዳዘዘው ኢያሱ እንዲሁ አደረገ ሙሴ ካዘዘው ሁሉ ምንም ምን አላስቀረም ፤

፲፮፤ ወነሥአ ኢያሱ ኵሎ ደወለ ምድሮሙ ዘመንገለ አድባር ወኵሎ ምድረ አዴብ ወኵሎ ጎሶም ወአንቃላቲሆሙ ወዘመንገለ ዓረቢሃ ወለኵሉ ደብረ እስራኤል ወታሕታዮኒ ደወሎሙ ዘመንገለ ደብር እምደብረ ኤኬል ፤

ኢያሱም በደጋ ያለ ያገራቸውን አውራጃና የአዴብና የጎሶምን አውራጃ ሁሉ ያዘ ፤ በምዕራብ በኩል ያለውን የእስራኤል አገር ሁሉ ከኤኬል ተራራ ጀምሮ ከደጋው በታች ያለውን አውራጃ ሁሉ ያዘ ፤

፲፯፤ ወየዐርግ እስከ ሴይር ወእስከ ገለዓድ ወአንቃላተ ሊባኖስ ዘመን

ገለ ደብረ አኤርሞን ወአኀዘሙ ለኵሎሙ ነገሥቶሙ ወቀተሎሙ ወአጥፍኦሙ ፤

ኢያሱ የያዘውም አገር እስከ ሴይርና እስከ ገለዓድ በአኤርሞን ተራራ በኩል እስከ ሊባኖስ አውራጃ ድረስ ያደርሳል ፤ የነዚህን አገሮች ነገሥታት ሁሉ ወግቶ አጠፋቸው ።

፲፰፤ ወኵንዱየ መዋዕለ ነበረ ኢያሱ ኀበ እሉ ነገሥት እንዘ ይትቃተሎሙ ፤

ኢያሱም ከሊህ ነገሥታት ጋራ እየተዋጋ ብዙ ዘመን ኖረ ፤ ኋላ አምስቱ ነገሥታት ብሎ ያመጣቸዋል ።

፲፱፤ ወአልቦ ሀገር እንተ ኢነሥኡ እስራኤል እንበለ ኤዋውያን ዘይነብሩ በገባዖን ወለኵሎሙ ነሥእዎሙ በቀትል ፤

በገባዖን የሚኖሩ ሰዎች ከያዙት በቀር እስራኤል እጅ ያላደረጉት አገር የለም አገሮቹን ሁሉ በጦርነት ያዙአቸው ።

፳፤ እስመ እግዚአብሔር አጽንዐ ልበሙ ለእስራኤል ውስተ ቀትል ከመ ይሥርውዎሙ አላ ከመ ያጥፍእዎሙ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ፤

እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው እልም ድርግም አድርገው ያጠፏቸው ዘንድ ነው እንዲ እንዳይራሩላቸው አሕዛብን በስልፍ ያጠፏቸው ዘንድ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልቡና አጽንቷልና ።

፳፩፤ ወሖረ ኢያሱ በእማንቱ መዋዕል ወአጥፍኦሙ ለአቂም ዘውስተ አድባር እምኬብሮን ወእምዳቤር ወእምአናቦት ወእምውስተ ኵሉ ደወሎሙ ለእስራኤል ወእምአድባረ ይሁዳ ምስለ አህጉሪሆሙ ፤

ኢያሱም በዚያ ወራት ዘመቻ ሒዶ ከኬብሮንና ከዳቤር ከአናቦት ጀምሮ በደጋ የሚኖሩ ኃያላኑን አጠፋቸው ፤ ከእስራኤል አውራጃ ከይሁዳም አውራጃ ያሉትን ሁሉ ከከተሞቻቸው ጋር አጠፋቸው ።

፳፪፤ ወአጥፍኦሙ ኢያሱ ወኢያተረፈ እምኔሆሙ ለዓቂም በማዕከለ እስራኤል ዘእንበለ ውስተ ጋዛ ወውስተ ጌት ወአዛጦን ዘተርፉ ፤

ኢያሱም በጋዛና በጌት በአዛጦንም ከቀሩት በቀር በእስራኤል መካከል ከኃያላኑ ምንም ሳይቀር አጠፋቸው ።

፳፫፤ ወነሥአ ኢያሱ ኵሎ ምድሮሙ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ፤

እግዚአብሔር ለሙሴ እንዳዘዘው ኢያሱም የአሕዛብን አገራቸውን ሁሉ እጅ አደረገ ።

ወወሀቦሙ ኢያሱ ርስቶሙ ለእስራ ኤል ዘከመ ክፍሎሙ በበነገዶሙ ወአ ዕረፈት እንከ ምድር እምቀትል ፤

ኢያሱም ለእስራኤል በየወገና ቸው እንደየእጣቸው ርስታቸ ውን ሰጣቸው ፤ ከዚህ በኋላ ምድር ከሰልፍ (ከጦርነት) አረ ፈች ።

## ምዕራፍ ፲፪

፩፤ ወእሉ እሙንቱ ነገሥት ዘቀተ ልዎሙ ደቂቀ እስራኤል ወወረስ ዎሙ ምድሮሙ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ሠርቀ ፀሐይ እምቈላተ አርኖን እስከ ደብረ አኤርሞን ወኵሉ ምድረ ዓረባ ዘመንገለ ጽባ ሒሁ ፤

ከአርኖን ቈላ ጀምሮ እስከ ዓረ ባና እስከ አኤርሞን ተራራ ድረስ በፀሐይ መውጫ በዮር ዳኖስ ማዶ የእስራኤል ልጆች ወግተው አገራቸውን የወረሷ ቸው የአሕዛብ ነገሥታት እኒህ ናቸው ፤

፪፤ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘይነብር ውስተ ሐሴቦን ወይኴንን እምአር ኖን እንተ ሀለወት ውስተ ቈላት ዘ፩ዱ ኅብር ወመንፈቀ ገለዓድ እስከ ኢያቦቅ ደወሎሙ ለደቂቀ አሞን ፤

ከነዚህም አንዱ በሐሴቦን የሚ ኖር አንድ ወገኑ ቈላ ከሆነ ከአ ርኖን እና ከገለዓድ እኩሌታ ጀምሮ የአሞን ልጆች ድንበር እስከሚሆን እስከ ኢያቦቅ ድረስ የሚገዛ ሴዎን ነው ፤

፫፤ ወዓረባ ወእስከ ባሕረ ኬኔሬብ ዘመንገለ ጽባሕ ወእስከ ባሕረ ዓረባ ባሕረ ኤሎን እምጽባሒሁ እምፍ ኖት ዘመንገል አሴሞት ወእምቴማን እንተ መትሕተ አሴዶት ወፋስጋ ወደወሳ ፤

በምሥራቅ እስከአለ እስከ ኬኔ ሬብ ባሕር ድረስ በአሴሞት ካለ በምሥራቁ መንገድ ጀምሮ ከፋስጋና ከአሴዶት አውራጃ በታች ካለች ከቴማን ጀምሮ ይኸውም የጨው ባሕር ነው ፤ አውራጃዋንም ሁሉ የሚገዛ ሴዎን ነው ፤

፬፤ ወአግ ንጉሠ ባሳን ዘተርፈ እምኔ ሆሙ ለእለ ያርብሀ እለ ይነብሩ ውስተ አስጣሮት ወበእንድራይን ፤

ሁለተኛው በእንድራይንና በአ ስጣሮት ከሚኖሩ አርበኞች ወገን የቀረ የባሳን ንጉሥ አግ ነው ፤

፭፤ ወመስፍን ውእቱ ላዕለ አድባረ አኤርሞን ወካሴኬ ወለኵሉ ባሳን እስከ አድዋለ ጌርጌሲ ወመከት ወመንፈቀ ገለዓድ ደወሉ ለሴዎን ንጉሠ ሐሴቦን ፤

እርሱም በአኤርሞን እና በካ ሴኬ አውራጃ እስከ ጌርጌሲና መከት አውራጃ ድረስ የሐሴቦን ንጉሥ የሴዎን አውራጃ እስከ ምትሆን እስከ ገለዓድም እኩ

ሌታ ድረስ ለባሳን ሁሉ ገዥ ነበረ ፤

፮፡ ሙሴ ቀኍልዔሁ ለእግዚአብሔር ወደቂቀ እስራኤል ቀተልዎሙ ወወሀቦሙ ርስቶሙ ሙሴ ኪያሃ ምድረ ለሮቤል ወለጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ፤

እነዚህንም የእግዚአብሔር ባለ ሟል ሙሴና የእስራኤል ልጆች አጠፏቸው ፤ ያችንም አገር ሙሴ ለሮቤልና ለጋድ ልጆች ለምናሴም ነገድ እኩሌታ ሰጣ ቸው ፤

፯፡ ወእሉ እሙንቱ ነገሥተ ምድረ ከነዓን ዘቀተልዎሙ ኢያሱ ወደቂቀ እስራኤል በማዕዶተ ዮርዳኖስ በመ ንገለ ባሕረ በለገድ ውስተ ገጻሙ ለሊባኖስ ወእስከ ደብረ ኤሌኬ ዘየ ዓርግ ውስተ ሴይር ፤

ኢያሱና የእስራኤል ልጆች በሊ ባኖስ ቈላ በበለገድ ባሕር አጠ ገብ ወደሴይር በሚደርስ በኤ ሌኬ ተራራ የገደሏቸው የከነዓን ነገሥታትም እሊህ ናቸው ፤

፰፡ ወወሀቦሙ ኢያሱ ይእተ ምድረ ለሕዝበ እስራኤል ወአውረሰሙ ርስተ በውስተ ደብርኒ ወበውስተ ገጻምኒ ወበዓረባ ወበአሴዶት ወበ አንቃላትኒ ወናጌብ ወበኬጤዎን ወበአሞሬዎን ወበከናኔዎን ወበፌር ዜዎን ወበኢያቡሴዎን ወበኤዌዎን ፤

ኢያሱም በዓረባና በአሴዶት በቈላና በደጋ በናጊብና በአው ራጃዎቿ ፤ በአሞሬዎንና በኬ ጤዎን ፤ በፌርዜዎንና በከናኔ ዎን ፤ በኤዌዎንና በኢያቡሴ ዎን በነዚህ አገሮች ያለውን አውራጃ ሁሉ ለእስራኤል ወገ ኖች ርስት አድርጎ አወረሳቸው ፤

፱፡ ንጉሠ ኢያሪኮ ወንጉሠ ጋይ እንተ መአኀዘ ቤቴል ፤

ኢያሱ ያጠፋቸው ነገሥታት እሊህ ናቸው የኢያሪኮ ንጉሥና የቤቴል መያያዣ (አጠገብ) የምትሆን የጋይ ንጉሥ ነው ፤

፲፡ ንጉሠ ኢየሩሳሌም ወንጉሠ ኬብ ሮን ፤

የኢየሩሳሌም ንጉሥና የኬብሮን ንጉሥ ፤

፲፩፡ ንጉሠ ኢያሪሞት ወንጉሠ ለኪ ሶን ፤

የኢያሪሞት ንጉሥ እና የለኪ ሶን ንጉሥ ፤

፲፪፡፲፫፡ ንጉሠ ኤሌም ወንጉሠ ጋዜር ንጉሠ ዳቤር ወንጉሠ ጋሲ ፤

የኤሌም ንጉሥ እና የጋዜር ንጉሥ የዳቤር ንጉሥና የጋሴ ንጉሥ ፤

፲፬፡፲፭፡ ንጉሠ ኤርሞት ወንጉሠ አራድ ንጉሠ ሉምና ወንጉሠ ኤዶ ላም ፤

የኤርሞት ንጉሥና የአራድ ንጉሥ የሉምና ንጉሥና የኤዶ ላም ንጉሥ ፤

፲፯:፲፰፡ ንጉሠ ኤዳ ወንጉሠ ኤጣ
ፋድ ንጉሠ አፌር ወንጉሠ አፌቀጠ
ሰሩት ፤

የኤዳ ንጉሥና የኤጣፋድ ንጉሥ
የአፌር ንጉሥና የአፌቀጠሰሩት
ንጉሥ ፤

፲፱:፳፡ ንጉሠ አሶር ወንጉሠ ስም
ዖን ንጉሠ መምሮት ወንጉሠ አዜፍ ፤

የአሶር ንጉሥና የስምዖን ንጉሥ
የመምሮት ንጉሥና የአዜብ
ንጉሥ ፤

፳፩:፳፪፡ ንጉሠ ቃሌስ ወንጉሠ ዘቃቅ
ንጉሠ ማርዶት ወንጉሠ የዴቆም
ዘኬርሜል ፤

የቃሌስ ንጉሥና የዘቃቅ ንጉሥ
የማርዶት ንጉሥና የኬርሜል
ዕፃ የምትሆን የዴቆም ንጉሥ ፤

፳፪፡ ፳፫፡ ንጉሠ ኤዶር ዘፌናድር
ንጉሠ ሐጌ ዘጋልያ ወንጉሠ ቴርሳ ፤

የፌናድር ዕፃ የምትሆን የኤዶር
ንጉሥ የጋልያ ዕፃ የምትሆን
የሐጌ ንጉሥና የቴርሳ ንጉሥ
ናቸው ፤

፳፬፡ እሉ ኵሎሙ ነገሥት ፴ወ
፩ቱ ፤

እስራኤል ያጠፏቸው ሃያ ዘጠኙ
ነገሥተ አሕዛብ እሊህ ናቸው ፤
አንድም እስራኤል ያጠፏቸው
የአሕዛብ ነገሥታት እሊህ ሃያ
ዘጠኙ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፲፫

፩፡ ወልሕቀ ኢያሱ ውኅለፈ መዋዕ
ሊሁ ፤

ኢያሱም አረጀ (ሸመገለ)፤ የሕ
ፃንነቱም ወራት አለፈ ፤

ወይቤሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ናሁ
ኀለፈ መዋዕሊከ ለከ ወተርፈት
ምድር ብዝኀት ዘኢተዋረሱ ፤

እግዚአብሔርም ኢያሱን እነሆ
የሕፃንነትህ ወራት አለፈ፤ እስ
ራኤል ያልወረሷትም ብዙ ሀገር
ቀረች አለው ፤

፪፡ ወዛቲ ይእቲ ምድር እንተ ተር
ፈት ደወሎሙ ለፍልስጥኤም ወለጌ
ሴሪ ወለከናኔዎን ፤

እስራኤል ሳይወርሷት የቀረች
አገርም ይህች ናት፤ የፍልስጥኤ
ምና የጌሴሪ የከናኔዎንም አው
ራጃ ናት ፤

፫፡ እምበድው ዘመንገለ ገጸ ግብፅ
እስከ ደወሎሙ ለአቃሮን ዘመንገለ
ጸጋሞሙ ለአሞሬዎን ዘይትኌለቍ
ለ፭ቱ በሐውርተ ፍልስጥኤም ፤

በግብጽ በኩል ካለው ምድረ
በዳ ጀምሮ ካምስቱ የፍልስጥ
ኤም አገሮች ጋር እስከሚቆ
ጠረው በአሞሬዎን በስተግራ
እስካለው እስከ አቃሮን አው
ራጃ ድረስ ያልወረሷት አገር
ይች ናት ፤

ለጋዛ ወለአዛጦን ወለአስቀሎና ወለ ጌት ወለአቃሮን ወለኤዊ እምቴ ማን ፤

አምስቱ በሐውርተ ፍልስጥኤም ያለውን ይተረትራል ፤ እሊህም ጋዛና አዛጦን አስቀሎናና ጌት አቃሮንና ከቴማን ቀጥሎ የም ትገኝ ኤዊ ናቸው ፤

፬፤ ወኵሉ ምድረ ከነዓን ዘቅድመ ጋዛ ወሲዶናዊ እስከ ጤፌቅ ወእስከ አድዋሊሆሙ ለአሞሬዎን ፤

በጋዛና በሲዶና አንፃር ያለ የከ ነዓን ምድር ሁሉ እስከ ጤፌ ቅና እስከ አሞሬዎን አውራጃ ያለ አገር ሁሉ ነው ፤

፭፤ ወኵሉ ምድረ ገድያድ ዘፍልስ ጥኤም ወኵሉ ሊባኖስ እምሠርቀ ፀሐይ ወእምገልገላ ዘመትሕተ ደብረ አኤርሞን እስከ ምብዋዓ ለኤማት ፤

የፍልስጥኤም ዕፃ እስከሚሆን እስከ ገድያድ አገር እስከ ሊባ ኖስ ሁሉ ከፀሐይ መውጫ ከአ ኤርሞን ተራራ በታች ካለ ከገ ልገላ ጀምሮ እስከ ኤማት መግ ቢያ ድረስ ነው ፤

፮፤ ወኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ አድባር እምሊባኖስ እስከ ሙአለ ሴሬት ዘማይም ዘፎሚም ወኵሉ ሲዶና እለ አነ አጠፍኦሙ እምቅ ድመ ገጸሙ ለእስራኤል በከመ እቤለከ ፤

ከሊባኖስ ጀምሮ የፎሚም ዕፃ እስከምትሆን እስከማይም ክፍል እስከ ሴሬት መያያዣ ድረስ በደጋ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ናቸው ፤ እኔ እንደነገርኩህ ከእ ስራኤል ፊት የማጠፋቸው እስከ ሲዶና ሁሉ ድረስ ነው ፤

፯፤ ወይእዜኒ ክፍሎሙ ዛተ ምድረ ወአስተዋርሰሙ ለተስዓቱ ሕዝብ ወለመንፈቀ ሕዝብ ዘምናሴ እምዮር ዳኖስ እስከ ባሕር ዓቢይ ዘመንገለ ዓረበ ፀሐይ ትሁቦሙ ወይከውኖሙ ወሰኖሙ ባሕር ዓቢይ ፤

አሁንም ይህችን አገር አካፍላ ቸው ለዘጠኙ ነገድና ለምናሴ ነገድ እኩሌታ አውርሳቸው ፤ ከዮርዳኖስ ጀምሮ ከፀሐይ መግ ቢያ እስካለ እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ስጣቸው ፤ ወሰናቸውም (ድንበራቸው) ታላቁ ባሕር ይሁ ናቸው አለው ፤

፰፤ ወለእልክቱ ፪ቱ ነገድ ዘሮቤል ወዘጋድ ወለመንፈቀ ነገደ ምናሴ ወሀቦሙ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአ ብሔር በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመን ገለ ሠርቀ ፀሐይ ፤

ለነዚህ ለሁለቱ ለሮቤልና ለጋድ ወገኖች ለምናሴም ነገድ እኩ ሌታ በፀሐይ መውጫ በዮርዳ ኖስ ማዶ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሙሴ አወረሳቸው ፤

፱፤ እምአሮኤር እንተ ውስተ ማዕከለ ቈላት ወኵሉ ሚሶር እምዴቦን ፤

በቈላ መካከል ባለች አገርና በአርኖን ወንዝ ማዶ ካለች ከአሮኤር ጀምሮ ከዴቦንም ክፍል ሚሶር የተባለውን አገር ሁሉ አወረሳቸው ፤

፲፤ ወኵሎ አህጉረ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘነግሠ በሐሴቦን እስከ ደወሎሙ ለደቂቀ አሞን ፤

በሐሴቦን የነገሠ የአሞሬዎን ንጉሥ የሴዎንን አገሮች ሁሉ እስከ አሞን ልጆች አውራጃ ድረስ ሰጣቸው ፤

፲፩፤ ወለገለዓድ ወለደወሎሙ ለጌሴሪ ወለመከጢ ወለኵሉ አድባረ አኤርሞን ወኵሉ ባሳን እስከ አካ ፤

ገለዓድን የጌሴሪንና የመከጢን አውራጃ የአኤርሞንንም ደጋውን ሁሉ ባሳንን ሁሉ እስከ አካ ድረስ ሰጣቸው ፤

፲፪፤ ወኵሎ መንግሥቶ ለአግ ዘባሳን ዘነግሠ በኢንድራይን ወበአስጣሮት ወውእቱ ዘተርፈ እምደቂቀ ለእለ ያርብሀ ወቀተሎሙ ሙሴ ወአውረሶሙ ፤

እምዘመዶሙ ሲል ነው፤ ይኸውም እነሱን አጥፍቶ ርስታቸውን ለእስራኤል ካወረሰባቸው ካርበኞች ወገን ነው ፤ በአስጣሮትና በእንድራይን የነገሠ የባሳን ንጉሥ የዓግን ግዛት ሁሉ ሰጣቸው ፤

፲፫፤ ወኢያጥፍእዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለጌሴሪ ወለመከጢ ወነበሩ ንጉሠ ጌሴሪ ወመከጢ ውስተ ደቂቀ እስራኤል እስከ ዛቲ ዕለት ፤

የእስራኤል ልጆች ጌሴሪንና መከጢንን አላጠፏቸውም ስለዚህም የጌሴሪ ንጉሥና የመከጢ ንጉሥ እስከዚች ቀን ድረስ በእስራኤል መካከል ተቀመጡ ፤

፲፬፤ እንበለ ሌዊ አለ ኢነሥኡ መክፈልቶሙ እስመ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ውእቱ መክፈልቶሙ በከመ ይቤሎሙ እግዚአብሔር ፤

«ግዚአብሔር እኑ ክፍልከ ወርስትከ» ብሎ እንደነገራቸው እድል ፈንታቸው የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ነውና እጣቸውን ካልተቀበሉ ከሌዊ ነገድ በቀር ለሁሉም አወረሳቸው ፤

፲፭፤ ወወሀቦሙ ሙሴ ለነገደ ሮቤል በበሕዘቢሆሙ ፤

ሙሴ ለሮቤል ነገድም በየወገናቸው ሰጣቸው ፤

፲፮፤ ወኮነ ደወሎሙ እምአሮኤር እንተ መንገለ ቈላተ አርኖን ወአህጉርኒ ዘውስተ ቈላተ አርኖን ፤

በአርኖን በረሀ ካለ ከአሮኤር ጀምሮ በአርኖን ቈላ ያለው አገር ሁሉ አውራጃቸው ሆነ ፤

፲፯፤ ወኵሉ ሚሶር እስከ ሐሴቦን ወኵሎን አህጉር ዘሀለዋ ውስተ ሚሶር ወዴቦን ወቤሞን ወባአል ወአብያተ ሚኤልሞት ፤

እስከ ሐሴቦን ያለው የሚሶር አገር ሁሉ ዴቦንና ቤሞን ባአልና የሚኤልሞት አውራጃ ሁሉ አገራቸው ሆነ ፤

፲፰፤ ወባሳን ወበቄድሚን ወሬማት ፤

ባሳንና በቄድሚን ሬማትም አገራቸው ነው ፤

፲፱፤ ወቀርያትም ወሲባማ ወሴራዳት ወስዮን በደብረ ኤናብ ፤

ቀርያትምና ሲባማ ሴራዳትና በኤናብ ተራራ ያለ ስዮን አገራቸው ነው ፤

፳፤ ወቤተ ፌጎር ወኤሴዶት ወፋስጋ ወኤቢታና ወሴኖት ፤

ፌጎር የሚባል ጣዖት ያለበት ቦታ ኤሴዴት እና ፋስጋ ኤቢታና ሴኖት የተባሉት አገሮች ሁሉ ለእስራኤል ሆኑ ፤

፳፩፤ ወኵሎን አህጉረ ሚሶር ወኵሉ መንግሥተ ሴዎን ንጉሠ አሞሬዎን ዘቀተሎሙ ሙሴ ፤

የሚሶር አገሮችና ሙሴ ያጠፋቸው የአሞሬዎን ንጉሥ የሴዎን ግዛቶች ሁሉ የእስራኤል አገሮች ሆኑ ፤

ወለመሳፍንተ ምድያም ኤዊን ወሮባቅ ወሱር ወኡር ወሮቤ ወለመሳፍንተ ጸራልያ ወለእለ ይነብሩ ውስተ ስዮን ፤

የምድያምን ገዥዎች ኤዊንና ሮባቅን ሱርና ዑርን ሮቤንም የጸራልያንም ገዥዎች በስዮን የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ሙሴ አጠፋቸው ፤

፳፪፤ ወለበለዓም ወልደ ቢኦር ዘመቅስም ቀተልዎሙ በምዕር ፤

ሟርተኛ የሚሆን የቢኦር ልጅ በለዓምንም ከነዚያ ጋር ጨምረው ባንድነት አጠፏቸው ፤

፳፫፤ ወኮነ ደወሎሙ ለደቂቀ ሮቤል ዮርዳኖስ ወሰኖሙ ፤

የሮቤል ልጆች ድንበራቸው ወሰናቸው ዮርዳኖስ ሆነ ፤

ወዝንቱ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ሮቤል በበነገዶሙ ወአህጉሪሆሙኒ ፤

የሮቤል ልጆች በየወገናቸው እጣቸውና አገራቸው ይህ ነው ፤

፳፬፤ ወወሀቦሙ ሙሴ ለደቂቀ ጋድ በበነገዶሙ ፤

ሙሴ ለጋድም ልጆች በየወገናቸው ርስታቸውን ሰጣቸው ፤

፳፭፤ ወኮነ ደወሎሙ ኢያዜር ወኵሎን አህጉረ ገለዓድ ወመንፈቀ ምድረ ደቂቀ አሞን እስከ ዓራባ እንተ ቅድመ ገጸ አራድ ፤

ኢያዜር ድንበራቸው ሆነ ፤ የገለዓድን አገርና የአሞንን ልጆች

አገር እኩሌታ በአራድ አንፃር እስካለው እስከ ዓራባ ድረስ ሰጣቸው ፤

፳፮፤ ወእምሐሴቦን እስከ አራቦት እንተ መንገለ መሴፋ ወቦጣኒ ወማ ያን እስከ ደወሎሙ ለዴቦን ወአዳማ ፡፡

ከሐሴቦን ጀምሮ በመሴፋና በቦጣኒ አውራጃ እስካለ እስከ አራቦት፣ ከማያንም ጀምሮ እስከ ዴቦንና እስከ አዳማ አውራጃ ድረስ ሰጣቸው ፤

፳፯፤ ወአትርጋ ወዓባይን ዘትንብሬ ወሴኮታ ወሰፌን ፡፡

ከአትርጋ ጀምሮ የትንብሬ ዕፃ እስከምትሆን እስከ ዓባይንም ድረስ ሴኮታና ሰፌንንም ሰጣ ቸው ፤

ወባዕድኒ ዘተርፈ መንግሥቱ ለሴ ዎን ንጉሠ ሐሴቦን ወዮርዳኖስ ወሰ ኖሙ እስከ ፩ዱ ኀብር ዘባሕረ ኬኔ ሬት በማዕዶተ ዮርዳኖስ ጽባሐዊ ፡፡

የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን ከሚገ ዛው የቀረው አገርም ሁሉ ለነሱ ሆነ፣ በምሥራቅ በኩል ባለ በዮ ርዳኖስ ማዶ ያለ የባሕረ ኬኔ ሬት ዕፃ እስከምትሆን እስካንድ ወገን ድረስ ዮርዳኖስ ወሰና ቸው ነው ፤

፳፰፤ ወዝንቱ ውእቱ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ጋድ በበነገዶሙ ወሚጡ ዘባኖሙ ቅድሜ ፀሮሙ እስመ በበነ ገዶሙ ኮነ አህጉሪሆሙኒ ወደብረ አህጉሪሆሙኒ ፡፡

የጋድ ልጆች በየወገናቸው ዕድል ፈንታቸው ይህ ነው፣ አገ ራቸውም መንደራቸውም በየወ ገናቸው ሁኗልና ከጠላቶቻቸው ፊት ጀርባቸውን መልሰው አን ገታቸውን ቀልሰው ሸሹ ፤

፳፱፤ ወወሀቦሙ ሙሴ ለመንፈቀ ነገደ ምናሴ በበሕዘቢሆሙ ፡፡

ሙሴም ለምናሴ ነገድ እኩሌታ በየወገናቸው ርስት ሰጣቸው ፤

፴፤ ወኮነ ደወሎሙ እምሐናን ወኵሉ ባሳን ወኵሉ መንግሥተ ዓግ ንጉሠ ባሳን ወኵሎን አህጉረ ኢያኤር እለ ሀለዋ ውስተ ባሳን ፷ አህጉር ፡፡

ድንበራቸውም ከሐናን ጀምሮ የባሳን ንጉሥ ዓግ የሚገዛው ባሳ ንና በባሳን ያሉ ስሳ አገሮች የሆኑ የኢያኤር አውራጃዎች ሁሉ አገሮቻቸው ሆኑ ፤

፴፩፤ ወመንፈቀ ምድረ ገለዓድ ወአ ስጣሮት ወኤንድራይን አህጉረ መን ግሥቱ ለዓግ እለ ውስተ ባሳን ለደ ቂቀ ማኪር ትውልደ ምናሴ ወለ መንፈቆሙኒ ለደቂቀ ማኪር ዘት ውልደ ምናሴ በበሕዘቢሆሙ ፡፡

የገለዓድ አውራጃ እኩሌታ በባ ሳን ያሉ ዓግ ይገዛቸው የነበሩ አገሮች ኤንድራይንና አስጣሮ ትም ለምናሴ ልጅ ለማኪር ልጆች ርስት ሆኑ ፣ ከምናሴ

የተወለደ የማኪር ልጆች የኩሌ ቶቹ በየወገናቸው ርስታቸው ይህ ነው ፤

፴፪፤ እሉ እሙንቱ ዘአስተዋረሶሙ ሙሴ በአራቦት ዘሞዓብ በማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ጽባሒሁ ለኢያ ሪኮ ፤

በኢያሪኮ ምሥራቅ በዮርዳኖስ ማዶ የሞዓብ ክፍል በምትሆን በአራቦት ሙሴ ያወረሳቸው እሊህ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፲፬

፩፤ ወእሉ እሙንቱ እለ አስተዋረስ ዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በምድረ ከነዓን አልዓዛር ካህን ወኢያሱ ወልደ ነዌ ወመላእክተ ቤተ አበው ነገዶሙ ለእስራኤል ፤

በከነዓን አገር ለእስራኤል ልጆች ርስት ያካፈሏቸው እኒህ ናቸው፤ የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚ ሆን አልዓዛርና የነዌ ልጅ ኢያሱ የእስራኤል ነገድ አባቶች የቤት አለቆች ናቸው ፤

፪፤ በበመክፈልቶሙ ተዋረሱ በከመ አዘዘ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ ፱ቱ ነገድ ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ እማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤

እግዚአብሔር በሙሴ ቃል እን ዳዘዘ ዘጠኙ ነገድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ከዮርዳኖስ ማዶ ማለት ዮርዳኖስን ተሻግረው በየ ዕጣቸው ምድረ ርስትን ወረሱ ፤

፫፤ ወለሌዋውያንስ ኢወሀብዎሙ መክፈልቶሙ ፤

ለሌዋውያን ግን እድል ፈንታ ቸው ምድረ ርስትን አላካፈሏ ቸውም ፤

፬፤ እስመ ደቂቀ ዮሴፍ ፪ቱ ነገድ እሙንቱ ዘምናሴ ወዘኤፍሬም ፤

የዮሴፍ ልጆች ምናሴና ኤፍ ሬም ሁለት ነገድ ተብለው ተቈ ጥረዋልና ፤

ወኢወሀብዎሙ መክፈልቶሙ ምድረ ለሌዋውያን ዘእንበለ አህጉር ዘውስ ቴቶን ይነብሩ ዘፈለጡ ሎሙ ፤

ለሌዋውያን ግን ከሚኖሩባቸው ለይተው ከሰጧቸው አገሮች በቀር እድል ፈንታቸው የሚ ሆን ርስት አልሰጧቸውም ፤

፭፤ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ ከማሁ ገብሩ ደቂቀ እስራኤል ወተ ካፈሉ ምድረ ፤

የእስራኤል ልጆች እግዚአብ ሔር ሙሴን እንዳዘዘው አድር ገው ምድረ ርስትን ወረሱ ፤

፮፤ ወመጽኡ ደቂቀ ይሁዳ ኀበ ኢያሱ በገልገላ ወይቤሎ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ ቄኔዛዊ ለሊከ ተአምር ቃለ ዘይ ቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ብእሴ እግዚአብሔር በእንቲአየ ወአንተኒ ውስተ ቃዴስ በርኔ ፤

የይሁዳ ልጆች በገልገላ ሳለ ወደ ኢያሱ መጡ ፤ የቄኔዝ ወገን የሚሆን የዮፎኒ ልጅ ካሌብም

ኢያሱን እንዲህ አለው ፣ የእግ ዚአብሔር ቤተሰብ ለሚሆን ለሙሴ እግዚአብሔር ስለኔ የነ ገረውን ነገር አንተም በቃዴስ በርኔ ነበርክና ታውቃለህ ፤

፯፡ እስመ አርብዓ ዓም ሊተ አመ ፈነወኒ ሙሴ ቍልዔሁ ለእግዚአብ ሔር እምቃዴስ በርኔ ከመ ንርአያ ለዛቲ ምድር ፣

የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ ይህችን አገር እንሰልላት ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ የአ ርባ ዘመን ጉልማሳ ነበርኩ ፤

፰፡ ወዜነውዎሙ ነገረ ዘከመ ሐሊ ናሆሙ አኃውየ እለ ዐርጉ ምስሌየ ወአክሐድዎ ለልበ ሕዝብ ወአንሰ ገባእኩ እትልዎ ለእግዚአብሔር አምላክነ ፣

ከእኔ ጋር ምድረ ርስትን ለመ ሰለል የሔዱ ወንድሞቼ ልቡና ቸው ያሰበውን ክፉውን ነገር ነግረው የእስራኤልን ልቡና ምድረ ርስት አንገባም በማለት አስካዱ፣ እኔ ግን እንገባለን በማ ለት ጸንቼ ፈጣሪያችን እግዚአ ብሔርን በሕግ በአምልኮት እከተለው ዘንድ ወደሱ ተመለ ስኩ ፤

፱፡ ወመሐለ ሙሴ በይእቲ ዕለት እንዘ ይብል ምድር እንተ ውስቴታ ዐረገ አንተ ለከ ትከውን መክፈል ተከ ወለውሉድከ ለዓለም እስመ ገባእከ እትልዎ ለእግዚአብሔር አምላክነ ፣

ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮት እከተለው ዘንድ እሱን ወደ መከተል ተመ ልሻለሁና ሙሴ በዚያች ቀን ወደሷ የሔድኩባት አገር ኬብ ሮን ላንተና ለልጆችህ እድል ፈንታ ትሆናለች ብሎ ማለ ፤

፲፡ ወይእዜኒ ናሁ ፵ወ፭ቱ ዓም እም አመ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ ዘንተ ቃለ ወሖሩ እስራኤል ውስተ ገዳም ወይእዜኒ ናሁ ዮምኒ እንዘ ሰማንያ ወኃምስቱ ዓመት ሊተ ፣

አሁንም እግዚአብሔር ለሙሴ ይህን ቃል ከነገረው እስራኤል በምድረ በዳ ከኖሩ ወዲህ ያለው ዘመን አርባ አምስት ነው ለኔም ዛሬ ሰማንያ አምስት ዘመን ሁኖ ኛል (ሲሆነኝ) ፤

፲፩፡ ዓዲየ ጽኑዕ አነ ከመ አመ ይፌን ወኒ ሙሴ ከማሁ ጽኑዕ አነ ይእዜኒ ለወፂእ ውስተ ጸብዕ ወለአቲውኒ ፣

አሁንም ገና ከጉልበት ነኝ ፣ ሙሴ በላከኝ ጊዜ እንደ ነበርኩ አሁንም ወደዘመቻ ለመውጣ ትና ለመግባት ይቻለኛል ፤

፲፪፡ ወይእዜኒ እስእለከ ዘንተ ደብረ በከመ ይቤ እግዚአብሔር በይእቲ ዕለት እስመ ለሊከ ሰማዕከ ይእቲ አሚረ ዘንተ ቃለ ፣

በዚያች ቀን እግዚአብሔር ምድረ ርስትን አወርሳችኋለሁ

ብሎ እንደተናገረ ያን ጊዜ አንተ ሰምተሃልና አሁንም ይህ ችን ኬብሮንን ስጠኝ ብየ እለ ምንሃለሁ ፤

ወሰብአ አቂም ሀየ ሀለዉ ወኢህጉሪ ሆሙ፡ኒ ዓበይት ወጽኑዓት ወእመሰ ሀለወ እግዚአብሔር ምስሌየ አጠፍ አሙ በከመ ይቤለኒ እግዚአብሔር ፣

የአቂም ሰዎችም በዚያ በኬብ ሮን ተራራ አሉ ፣ አምባዎቻቸ ውም ፈጽመው የጸኑ ናቸው ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በረድ ኤት ከኔ ጋር ካለ ታጠፋቸዋ ለህ ብሎ እንደነገረኝ አሁንም አጠፋቸዋለሁ አለ ፤

፲፫፤ ወባረኮ ኢያሱ ለካሌብ ወልደ ዮፎኒ ወልደ ቄኔዝ ወሀቦ ኬብሮንሃ መክፈልቶ ፣

ኢያሱም የቄኔዝ ልጅ የሚሆን የዮፎኒ ልጅ ካሌብን መረቀው ኬብሮንንም እድል ፈንታ አድ ርጎ ሰጠው ፤

፲፬፤ ወበበይነ ዝንቱ ኮነት ኬብሮን ለካሌብ ወልደ ዮፎኒ ቄኔዛዊ መክ ፈልቶ እስከ ዛቲ ዕለት እስመ ተለዎ ለእግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ፣

የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔ ርን በሕግ በአምልኮት ተከት ሎዋልና ስለዚህ ነገር ኬብሮን እስከዚች ቀን ድረስ የቄኔዝ ወገን ለሚሆን ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ዕድል ፈንታ ሆነች ፤

፲፭፤ ወስማሰ ቀዲሙ ለኬብሮን ሀገረ አርጐብ ወደብረ አህጉር ይእቲ ለእለ ውስተ አቂም ወአዕረፈት ምድር እምቀትል ፣

ቀድሞ ግን የኬብሮን ስሟ የአ ርጐብ ሀገር ትባል ነበር ፣ በአ ቂም ላሉ ሰዎችም ያገራቸው መዲና ነበረች ከዚህ በኋላም አገራቸው በጦርነት ከመጋደል ዐረፈች ።

## ምዕራፍ ፲፭

፩፤ ወኮነ ደወሎሙ ለነገደ ይሁዳ በበሕዘቢሆሙ ዘመንገለ አዜብ ኀበ ደወለ ኤዶም እምገዳም ዘፂን ፣

የይሁዳ ነገድ በየወገናቸው የወ ረሱት በኤዶምያስ አውራጃ ባለ በአዜብ በኩል ፂን የሚባል እንጪት ካለበት ምድረ በዳ ጀምሮ ነው ፤

፪፤ እምጽንፈ ቴማን እስከ ፩ኅብር ዘባሕረ ኤሌቄ ወእምፍኖት እንተ ትወስድ ላዕለ ሊባ ፣

ከቴማን ዳርቻ ጀምሮ እስከ ባሕረ ኤሌቄ (እስከ ባሕረ ዔው) እስከ አንድ ወገኑ ድረስ ወደ ሊባ (ወደ ደቡብ) ከምትወስድ መንገድ ጀምሮ አውራጃቸው ሆነ ፤

፫፤ ወተሐውር እንተ ቅድመ አቅ ራቢን ወትወጽእ ላዕለ ኤናቅ ወተዓ ርግ እምሊባኖስ ላዕለ ቃዴስ በርኔ

ወትወጽእ ላዕለ አሥሮን ወተዐርግ ላዕለ ሠራዳ ወትወጽእ ላዕለ ዓረበ ቃዴስ ፤

መንገዷም ወደ አቅራቢን አን ፃር ትወስዳለች ፤ በኤናቅም በኩል ከሊባኖስ ወደቃዴስ በርኔ የምታደርስ ናት ፤ ከቃዴስ በርኔም ወደሠራዳ ትወስዳለች (ትደርሳለች) ፤ ከሠራዳም ወደ ቃዴስ ምዕራብ ትደርሳለች ፤

፬፤ ወተሐውር ላዕለ ኤልሞናን ወት ወጽእ ላዕለ ቈላተ ግብፅ ወይከውን ሞጻእቱ ለደወሉሙ ላዕለ ባሕር ወዝንቱ ውእቱ ደወሉሙ ዘመንገለ አዜብ ፤

ወደ ኤልሞናንና ወደግብፅ በረ ሀም ትደርሳለች (ሞጻእቱ ፍጻ ሜሁ ሲል ነው) ፤ ያገራቸው ፍጻሜም በባሕር ዔው አጠገብ ነው ፤ በአዜብ በኩል ድንበራ ቸው ይህ ነው ፤

፭፤ ወደወሉሙ ዘመንገለ ጽባሕ ኵሉ ባሕረ ኤሌቄ እስከ ዮርዳኖስ ወደ ወሉሙኒ ዘመንገለ መስዕ እም ፍኖት እንተ ኀበ ባሕር ወእም፩ ኅብር ዘዮርዳኖስ ፤

በምሥራቅ በኩልም ድንበራ ቸው ከባሕረ ኤሌቄ (ባሕረ ዔው) እስከ ዮርዳኖስ ድረስ ነው ፤ በሰሜንም በኩል ያለው ድንበራቸው ወደባሕረ ዔው ከሚወስደው መንገድ ጀምሮ ከዮርዳኖስም ካንድ ወገኑ ጀምሮ ነው ፤

፮፤ ወየዐርግ ደወሉሙ ዲበ ቤተ ግለ ዓም ወየኀልፍ ዲበ ባራ ወየዐርግ ላዕለ ሊቶንቤዖን ዘደወለ ሮጋቤል ፤

ድንበራቸው ወደቤተ ገለዓም ይደርሳል፤ ከዚያም በባራ አልፎ የሮጋቤል አውራጃ ወደሚሆን ወደሊቶንቤዖን ይደርሳል ፤

፯፤ ወየዓርግ ላዕለ ራብዕቱ ለቈላተ አኮር ወይወርድ ላዕለ ገልገላ እንተ ቅድመ ማዕዶተ አዳሚን እንተ መን ገለ አዜቡ ለቈላ ፤

ከአኮር ቈላም ካራተኛው ክፍል ይደርሳል፤ ከዚያም በቈላው በስ ተግራ ባለ በአዳሚን መሻገሪያ ፊት ለፊት ወዳለ ወደገልገላ ይደርሳል ፤

ወትወጽእ ላዕለ ነቅዓ ማየ ሄልዩ ወይ ከውን ሞፃእቱ ነቅዓ ሮጌል ፤

ከዚያም የሄልዩ ወሃ ምንጭ እስካለበት ቦታ ትሔዳለች ፍጻ ሜውም የሮጌል ምንጭ ነው ፤

፰፤ ወየዐርግ እንተ ቈላተ ወልደ ኤኖም እንተ መንገለ አዜባ ለኢያቡስ እንተ ይእቲ ኢየሩሳሌም ወይወጽእ ዳውራ ውስተ ርእሰ ደብር ዘሀለወ ቅድመ ቈላተ ኤኖም ዘኀበ ባሕር እንተ ውስተ ፩ኅብር ዘምድረ ራፋ ይን ዘመንገለ መስእ ፤

ይህችውም ኢየሩሳሌም ናት ፤ በኢያቡስ በስተግራ ወዳለ ወደ

ኤኖም ልጅ አውራጃ ትደርሳ
ለች ፤ በሰሜንም በኩል ኃያላኑ
በያዟት አገር በአንድ ወገንም
በባሕረ ዔው አጠገብ ባለ በሄኖን
በረኃ አንፃር ወዳለ ወደ ተራ
ራው ራስ ወደ ዳወራ ይደርሳል ፤

፱፤ ወይወስድ እምውእቱ ርእሰ ደብር
ላዕለ ነቅዓ ማይ ዘነፍቶ ወይበጽሕ
ውስተ ኤፍሮን ወይወስድ ላዕለ ኢያ
ቡኤል እንተ ይእቲ ሀገረ ኢያሪን ፤

ከዚህ ከተራራው ራስ ጀምሮ
ነፍቶ ወደሚባል ወሃ መፍለቂያ
ይደርሳል ፤ ወደኤፍሮንም ይደ
ርሳል ፤ ይህችውም ኢያሪን የም
ትባል አገር ናት ፤ ወደኢያቡኤ
ልም ይደርሳል ፤

፲፤ ወየኀልፍ ደወሎሙ እምኢያቡ
ኤል ላዕለ ባሕር ወየኀልፍ እንተ
ደወለ አስራቱስ እንተ መንገለ አዜባ
ለሀገረ ኢያሪም ወመስዓ ለከስሎን
ወይወስድ ላዕለ ሀገረ ኤልዩ ወየኀ
ልፍ ላዕለ ሊባ ፤

ወሰናቸውም ከኢያቡኤል ጀምሮ
ወደባሕሩ ይደርሳል፤ በኢያሪም
በስተግራ ወዳለች ወደአስራቱስ
አውራጃ ያልፋል፤ በከስሎን በስ
ተሰሜን በኩልም ወደ ኤልዩና
ወደ ሊባ አውራጃ ይደርሳል ፤

፲፩፤ ወይወጽእ ላዕለ አዜባ ለአቃ
ሮን ወይገብእ ላዕለ መስዕ ወይወጽእ
ዲበ ሰቆት ወየኀልፍ ላዕለ አዜብ ፤

በአቃሮን በስተግራ አልፎ ወደ
ሰሜኑ አውራጃ ይደርሳል ፤ በስ
ቆትም አልፎ ወደ ደቡብ ይሔ
ዳል ፤

ወይወጽእ ላዕለ ሌብና ወይከውን
ሞፃእቱ ለደወሎሙ ዲበ ባሕር ወደ
ወሎሙኒ ዘመንገለ ባሕር ዓቢይ
ባሕር ወሰኖሙ ፤

ወደሌብናም ይደርሳል ፤ «ሞፃ
እቱ» ፍጻሜሁ ሲል ነው ፤ ያገ
ራቸውም ፍጻሜ ባሕር ነው ፤
ስለዚህ በምዕራብ በኩል ወሰ
ናቸውና ድንበራቸው ታላቁ
ባሕር ነው ፤

፲፪፤ ወዝንቱ ውእቱ ወሰኖሙ ወደ
ወሎሙ ለደቂቀ ይሁዳ ዘዓውደሙ
በበሕዘቢሆሙ ፤

የይሁዳ ልጆች በየወገናቸው
በዙሪያቸው ያለ ወሰናቸውና
ድንበራቸው ይህ ነው ፤

፲፫፤ ወለካሌብ ወልደ ዮፎኒ ወሀቦ
መክፈልቶ በማዕከሎሙ ለደቂቀ
ይሁዳ በትእዛዘ እግዚአብሔር ወወ
ሀቦ ኢያሱ ሀገረ አስቦቅ ደብረ እሀ
ጉረ ኤናቅ እንተ ይእቲ ኬብሮን ፤

ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብም ኢያሱ
በእግዚአብሔር ትእዛዝ በይ
ሁዳ ልጆች መካከል እድል ፈን
ታውን ሰጠው ፤ ይኸችውም
ኬብሮን ናት ፤ የኃያላኑ አገ
ሮች መዲና የምትሆን አስቦቅ
የምትባለውን አገር ሰጠው ፤

፲፬፤ ወሠረዎሙ እምህየ ካሌብ
ወልደ ዮፎኒ ለሠለስቲሆሙ ደቂቀ

ኤናቅ ለጡቢ ወለጠሐሚ ወለአ
ከሚ ፤

የዮፎኒ ልጅ ካሌብም የኤናቅን ሦስቱን ልጆቹን ጡሲና ጠሐሚን አከሚንም አጠፋቸው ፡፡

፲፭፡ ወዐርገ እምህየ ካሌብ ላዕለ እለ ይነብሩ ውስተ ዳቤር ወስማ ለዳቤር ቀዲሙ ሀገረ መጽሐፍ ፤

ካሌብም ከኬብሮን በዳቤር ወደ ሚኖሩ አሕዛብ ዘመተ ፤ የዳቤርም የጥንት ስሟ የወግ የታሪክ አገር ትባል ነበር ፡፡

፲፮፡ ወይቤ ካሌብ ዘነሥአ ወቀተላ ለሀገረ መጽሐፍ ወአስተጋብአ እሁቦ አስካሃ ወለትየ ትኩኖ ብእሲተ ፤

ካሌብም የወግ የታሪክ የሆነችውን አገር ወግቶ እጅ ላደረጋት ሰው ሚስት ትሆነው ዘንድ ልጄ አስካን እሰጠዋለሁ አለ ፡፡

፲፯፡ ወነሥአ ጎቶንያል ወልደ ቄኔዝ እኁሁ ለካሌብ ወወሀቦ አስካሃ ወለቶ ትኩኖ ብእሲተ ፤

የካሌብ ወንድም የቄኔዝ ልጅ ጎቶንያል ያችን ሀገር ወግቶ እጅ አደረጋት ፤ ልጁ አስካንም ሚስት ልትሆነው ሰጠው ፡፡

፲፰፡ ወእምዝ ሶበ ለሐዊር ተማከረቶ እንዘ ትብል እስእሎ ለአቡየ ገራህተ ወጸርሐት በዲበ አድግ ወይቤላ ካሌብ ምንተ ኮንኪ ፤

ከዚህ በኋላ (ተንሥአት ያለበት ነው) ፤ ለመሔድ በተነሣች ጊዜ ከባሏ ጋር ተማከረች ፤ አምከረቶ ይላል ፤ ባሏን አማከረችው ፤ አባቴን ጉልት ስጠኝ ብዬ ልለምነው ብላ ስለዚህም በአህያው ላይ (በበቅሎው) ላይ ሁና አለቀሰች ፤ ካሌብም ምን ሆንሽ አላት ፡፡

፲፱፡ ፳፡ ወትቤሎ ሀበኒ በረከተ እስመ ውስተ ምድረ አዜብ ፈነውከኒ ወመጠውከኒ ሀበኒ በታኔስሃ ወወሀባ ጎኒታላን እንተ ላዕሉ ወጎኒታላን እንተ ታሕቱ እምርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ይሁዳ ፤

ወደ በረሀ አገር ሰደኸኛልና በበረሀ አገር ላለ ሰውም ሰጥተኸኛልና በታኔስን ጉልት ስጠኝ አለችው ፤ ከይሁዳ ልጆች ርስት ላይኛይቱን ጎኒታላንና ታችኛዪቱን ጎኒታላን ሰጣት ፡፡

፳፩፡ ወኮነ አህጉሪሆሙ ለነገደ ደቂቀ ይሁዳ ኀበ ደወለ ኤዶም ወአዜብ በሴልኤል ወአራ ወአሶር ፤

የይሁዳ ልጆች አገሮቻቸው በኤዶም አውራጃ በአዜብ በኩል በሴልኤል እና አራ አሶርም ነው ፡፡

፳፪፡ ፳፫፡ ወኢቃም ወራግማ ወአሩሄል ወቃዴስ ወአሶርዮስም ወመናን ፤

ኢቃምና ራግማ አሩሄልና ቃዴስ አሶርዮስምና መናን ፡፡

፳፬፡ ወበልማናን ወአእፃዲሆን ወሀገረ አሴሮም እንተ ይእቲ አሶር ፤

በልማናንና አውራጃቸው ናቸው ይኸችውም አሶር ናት አሴሮም የምትባለው ሀገርም አገራቸው ናት ፤

፳፭፡ ፳፮፡ ወሶምአ ወሞላዳ ወሴር ወቤፋላድ ፤

ሶምአና ሞላዳ ሴርና ቤፋላድ ናቸው ፤

፳፯፡ ፳፰፡ ወኮላሲአዳ ወቤርሳህ ወአዕፃዳቲሆን ባላ ወባቆብ ወደብራቲሆን ፤

ኮላሲአዳና ቤርሳህ ከአውራጃዎቻቸው ጋራ ባላና ባቆብም ከመሰማሪያዎቻቸው ጋራ ናቸው ፤

፳፱፡ ፴፡ አሶም ወኤለበሄዳድ ወቤቴል ወኤርማ ወሴቄላቅ ወመክሮን ወሰቱና ፤

ኤለበሄዳድና አሶም ፤ ኤርማና ቤቴል ፤ መክሮንና ሴቄላቅ ሰቱና ናቸው ፤

፴፩፡ ወላበስ ወሳሌ ወኤሞት ፳ወ፱ቱ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን በውስተ ሐቅል ፤

ላቦስና ሳሌ ኤሞትም በምድረ በዳ ካሉ ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር ሃያ ዘጠኝ አገሮች የነሱ ናቸው ፤

፴፪፡ ፴፫፡ ወአስጥሃል ወአራ ወአሣ ወራሚና እንተ ላዕሉ ወኢዳዳት ወመሐስን ፤

አስጥሃልና አራ ፤ ዓሣና በላይ ያለች ራሚና ፤ ኢዳዳትና መሐስን ናቸው ፤

፴፬፡ ፴፭፡ ወኤርሞት ወኤዶላም ወአምራ ወሰአክ ወሐዜቃ ወሴቃርም ወጋዴር ወዳቤር አሥሩ ወዓርባዕ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፤

ኤርሞትና ኤዶላም ፤ ሰአክና አምራ ፤ ሐዜቃና ሴቃርም ፤ ጋዴርና ዳቤር ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር እሊህ አሥራ አራት አገሮች የነሱ ናቸው ፤

፴፮፡፴፯፡ ሲና ወአዶሳን ወመገጽገጽ ወአዶላል ወመሴፋ ወይቃሩል ወመኬሳ ፤

አዶሳንና ሲና፤ አዶላልና መገጽገጽ፤ መሴፋና ይቃሩል መኬሳ ናቸው ፤

፴፰፡፴፱፡ ወበሴዶት ወይዴሃ ወዳልያ ወኮብራ ወመሐኮስ ፤

በሴዶትና ይዴሃ ፤ ዳልያና ኮብራ ማኮስ ናቸው ፤

፵፡ ወጋዶራ ወበጋዲያል ወኖማን ወመቄዶም አሥሩ ወስሱ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፤

ጋዶራና በጋዲያል ፤ ኖማንና መቄዶም ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር እሊህ አሥራ ስድስት አገሮች የነሱ ናቸው ፤

፵፩፡፵፪፡ ሌምና ወኢተቅ ወአኖክ ወአድና ወናሴብ ወኤላም ፤

ኢተቅና ሌምና፣ አኖክና አድና፣ ናሴብና ኤላም የነሱ ናቸው ፤

፵፫፡ ወአቀኍዛም ወራሴር ወኤሎም ፱ቱ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፤

አቀኍዛምና ራሴር ኤሎምም ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር እነ ዚህ ዘጠኙ አገሮች የነሱ ናቸው ፤

፵፬፡ አቃሮን ወአዕፃዳቲሃ ወደብራቲሃ ፤

አቃሮን ከአውራጃዋና ከመሰማሪያዋ ጋር የነሱ ናት ፤

፵፭፡ እምአቃሮን ወጌማ ወኵሉ ዘህለወ ቅሩበ አሴዶት ወአዕፃዳቲሆን ፤

ከአቃሮንና ከጌማ ጀምሮ ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር በአሴዶት አቅራቢያ ያለው አገር ሁሉ አገራቸው ሆነ ፤

፵፮፡ አሴዶት ወአዕፃዳቲሃ ወደብራቲሃ ወጋዛ ወአዕፃዳቲሃ ወደብራቲሃ እስከ ፈለገ ግብፅ ወባሕር ዓቢይ ወሰኑ ፤

አሴዶት ከአውራጃዋና ከመሰማሪያዋ ጋር ፣ ጋዛ ከአውራጃዋና ከመሰማሪያዋ ጋር እስከ ግብፅ ወንዝ ድረስ አገራቸው ሆነ ፣ ወሰኑም እስከ ታላቁ ባሕር ድረስ ነው ፤

፵፯፡፵፰፡ ወአድባረ ሳምርሂ ኤዬቴር ወወስካ ወፌና ወሀገረ መጽሐፍ ይእቲ ዳቤር ፤

የኤዬቴር የሣምርና የወስካ ፣ የፌናንም ተራራዎች ይህችውም የወግ የታሪክ ሀገር የምትሆን ዳቤር ናት ፤

፵፱፡፶፡ ወአኖን ወሴቁማ ወኤሱም አሥሩ ወአሐቲ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፤

አኖንና ሴቁማ ኤሱም ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር አሥራ አንድ አገሮች የነሱ ናቸው ፤

፶፩፡፶፪፡ ኤሬም ወራምና ወሶርማ ወኢያማይን ወቤቱቁ ወፍቁሕ ወኤውማ ፤

ኤሬምና ራምና ሶርማም ቤቱቁና ኢያማይን ኤውማና ፍቁሕ፤

፶፫፡፶፬፡ ወህገረ አርጎብ እንተ ይእቲ ኬብሮን ወሶሬት ተስዑ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፤

ይኸችውም ኬብሮን ናት ፣ አርጎብና ሶሬት ከመሰማሪያቸው ጋር እነዚህ ዘጠኝ አገሮች ናቸው ፣ (አገሮቻቸው) ሆኑ ፤

፶፭፡፶፮፡ ማሆር ወኬርሜል ወአዜብ ወኢጦን ወኢያሬዩል ወኢያሪቀም ወዘቃይን ፤

ማሆርና ኬርሜል ፣ አዜብና ኢጦን፣ ኢያሬዩልና ኢያሪቀም ዘቃይን ፤

፶፯፥፶፰፥ ወጋባ ወተምና ተሰዑ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን አብዋ ወተሱር ወጌዳር ፣

ጋባና ተምና እነዚህ ዘጠኙ አገሮች ከመሰማሪያቸው ጋር አብዋና ተሱር ጌዳርም አገሮቻቸው ናቸው ፤

፶፱፥ ወሜጌዶት ወቤታንዎ ወኤቱም ስሱ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፣

ሜጌዶትና ቤታንዎ ኤቱም ከመሰማሪያቸው ጋር ስድስቱ አገሮች የነሱ ናቸው ፤

፷፥ ቶቈ ወኤፍራታ እንተ ይእቲ ቤተልሔም ወፋጎር ወኤጣን ወቱላን ወጠጠን ወሶብሄ ወቃሬ ወጌሌም ወኤቴር ወመኖክ አሥሩ ወአሐቲ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፣

ይኸቸውም ቤተልሔም ናት ፣ ኤፍራታና ቶቈ፣ ፋጎርና ኤጣን ቱላንና ጠጠን፣ ሶብሔና ቃሬ፣ ጌሌም እና ኤቴር መኖክም ከመሰማሪያቸው ጋር ፲፩ አገሮች ናቸው ፤

፷፩፥ ቀርያትበዓል እንተ ይእቲ ሀገረ ኢያሪም ወሶቤታ ክልኤቲ አህጉር ወደብራቲሆን በልዳንስ ወተራብአም ወኤምን ፣

ይኸቸውም ኢያሪም የምትባል አገር ናት ፣ ቀርያትበዓልና ሶቢታ ከአውራጃቸው ጋራ ሁለቱ አገሮች በልዳንስና ተራብአምና ኤምን አገሮቻቸው ናቸው ፤

፷፪፥ ወሴኬዎዛን ወናፍለዛን ወሰሎን ወአቃዱሳ ሰብዑ አህጉር ወአዕፃዳቲሆን ፣

ሴኬዎዛንና ናፍለዛን ሶሎንና አቃዱሳ ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር ሰባት አገሮች የነሱ ናቸው ፤

፷፫፥ ወለኢያቡሴዎን እለ ይነብሩ ውስተ ኢየሩሳሌም ስእንዎሙ ደቂቀ ይሁዳ አጥፍአቶሙ ወነበሩ ኢያቡሴዎን ውስተ ኢየሩሳሌም እስከ ዛቲ ዕለት ፣

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢያቡሴዎን የተባሉ አሕዛብን የይሁዳ ልጆች ማጥፋት ተሳናቸው የኢያቡሴዎንም ወገኖች እስከዚህች ቀን ድረስ በኢየሩሳሌም ኖሩ ።

## ምዕራፍ ፲፮

፩፥ ወኮነ ደወሎሙ ለደቂቀ ዮሴፍ እምዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ እምጽባሒሁ ወየዐርግ እምኢያሪኮ ላዕለ አድባር ዘውስተ ገዳም ውስተ ቤቴል ሎዛ ፣

የዮሴፍ ልጆች ድንበራቸው በኢያሪኮ አንፃር ካለ ከዮርዳኖስ ከምሥራቁ ጀምሮ ነው ፣ ከኢያሪኮም ሎዛ በተባለች ቤቴል ወዳለ ምድረ በዳ ይደርሳል ፤

፪፥ ወይወፅእ እምቤቴል ሎዛ ወየኀልፍ ላዕለ ደወለ ኬሮንቲ ፣

ሎዛ ትባል ከነበረ ከቤቴል አንስቶ በኬሮንቲ አውራጃ በላይ ይወጣል ፤

፫፤ ወይነልፍ ኀበ ፫ቱ አፍላግ ውስተ ደወሎሙ ለቤቶሮን ዘታሕታይ ወይከውን ሞፃዕቱ ላዕለ ባሕር ፤

በቈላ ባለ በቤቶሮን አውራጃ አድርጎ ፫ት ወንዞች ወደ አሉበት ወደ ኬሮንቲ አውራጃ ይደርሳል ፤ ፍጻሜውም የኤርትራ ባሕር ነው ፤

፬፤ ወተዋረሱ ደቂቀ ዮሴፍ ኤፍሬም ወምናሴ ፤

የዮሴፍ ልጆች ኤፍሬምና ምናሴ ይህን አገር ተካፍለው ወረሱ ፤

፭፤ ወኮነ ደወሎሙ ለኤፍሬምኒ በበ ሕዘቢሆሙ እምጽባሒሃ ለአጣሮት ወኤሮሳ ወቤቶሮን እንተ ላዕሉ ወጋዛራ ፤

የኤፍሬም ልጆች በየወገኖቻቸው የወረሱት አውራጃቸው ከአስጣሮትና ከኤሮሳ ከላይኛዪቱ ቤቶሮንና ከጋዛራ ምሥራቅ ጀምሮ ነው ፤

፮፤ ወይነልፍ ላዕለ ባሕር እመሰአ ለቴርማ ወይነልፍ ላዕለ ጽባሕ ዲበ ቴርናታ ወውስተ ኤላስ ወይነልፍ እምጽባሕ ውስተ ኢያኖክ ወውስተ መራካ ወአጣሮት ወአዕፃዳቲሆን ፤

ከቴርማ ሰሜን ጀምሮ ወደ ኤርትራ ባሕር ይደርሳል ፤ በኤላስና በቴርናታም ወደ ምሥራቁ ይደርሳል ፤ ከምሥራቁም ወደ ኢያኖክና ወደ መራካ ወደ አጣሮትም ወደ አውራጃቸውም ይደርሳል ፤

፯፤ ወይበውእ ዲበ ኢያሪኮ ወይወፅእ ዲበ ዮርዳኖስ ፤

ከዚያም ወደ ኢያሪኮ ይደርሳል (ይገባል) ፤ ከኢያሪኮም ወደ ዮርዳኖስ ይወስዳል ፤

፰፤ ወእምጣፉ የሐውር ላዕለ ባሕር ዲበ ኬልቃና ወይከውን ሞፃዕቱ ዲበ ባሕር ወዝንቱ፡ ውእቱ ርስቶሙ ለሕዝበ ኤፍሬም በበሕዘቢሆሙ ፤

ከጣፉም በኬልቃና ላይ ወደ ባሕሩ ይደርሳል ፤ ፍጻሜውም የኤርትራ ባሕር ነው ፤ የኤፍሬም ነገዶች በየወገናቸው የወረሱት ርስታቸው ይህ ነው ፤

፱፤ ወአህጉርኒ እለ ፈለጡ ለደቂቀ ኤፍሬም በውስተ ማዕከለ ርስቶሙ ለደቂቀ ምናሴ ኵሉ አህጉሪሆሙ ወሙፋራቲሆሙ ፤

በምናሴ ልጆች ርስት መካከል ለኤፍሬም ልጆች የለየላቸው አገሮች ከመሰማሪያቸው ጋር አገሮቻቸው ሁሉ እነዚህ ናቸው ፤

፲፤ ወኢያጥፍአሙ ኤፍሬም ለከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስተ ጋዜር ወነበሩ ከናኔዎን ውስተ ኤፍሬም እስከ ዮም ወኮኑ መጸብሐ ፤

የኤፍሬም ልጆች በጋዜር የሚኖሩ የከናኔዎንን ወገኖች አላጠፏቸውም ፤ እነዚህም እስከ ዛሬ ድረስ በኤፍሬም ዕጣ ውስጥ ለኤፍሬም ልጆች ገባር ሁነው ኖሩ ።

## ምዕራፍ ፲፯

፩፤ ወኮነ ደወሎሙ ለነገደ ደቂቀ ምናሴ እስመ ውእቱ በኵሩ ለዮሴፍ ወማኪር በኵሩ ለምናሴ አቡሁ ለገለዓድ እስመ ብእሲ መስተቃትል ውእቱ ኮነ ሎቱ ገለዓድ ወባሳን ፤

የዮሴፍ የበኸር ልጅ ምናሴ ነውና የምናሴ ልጆች ደንበራቸው ይህ ነው ፤ ለምናሴ ለበኸር ልጁ ለገለዓድ አባት ለማኪርም አርበኛ ነውና ገለዓድ ከባሳን ጋር ለእርሱ ዕጣ ሆነ ፤

፪፤ ወኮነ ለደቂቀ ምናሴ እለ ተርፉ በበሕዘቢሆሙ ለደቂቀ ኢያዜ ወለደቂቀ ቄሌዚ ወለደቂቀ ኢያርያል ወለደቂቀ ኢሐኬም ወለደቂቀ አፌር እሉ ተባዕቶሙ በበሕዘቢሆሙ ፤

ለቀሩትም ለምናሴ ልጆች በየወገናቸው ለቄሌዚ ልጆችና ለኢያዜ ልጆች ፤ ለኢሐኬም ልጆችና ለኢያርያል ልጆች ፤ ለአፌርም ልጆች ርስታቸው (ዕጣቸው) ሆነ ፤ በየወገናቸው ወንዶቹ እኒህ ናቸው ፤

፫፤ ወለሰለጸዓድ ወልደ አፌር አልቦ ደቂቅ ዘእንበለ አዋልድ ወዝንቱ ውእቱ አስማቲሆን መሐላ ወኑኅ ወሔግላ ወሜልካ ወቴርሳ ፤

ለአፌር ልጅ ለሰለጸዓድም ከሴቶች ልጆች በቀር ወንድ ልጅ አልነበረውም ፤ የሴቶቹ ልጆቹ ስማቸውም መሐላ ኑኅ ሄግላ ሜልካ ቴርሳ ነው ፤

፬፤ ወቆሙ ቅድመ አልዓዛር ካህን ወቅድመ ኢያሱ ወቅድመ መላእክት ወይቤላ እግዚአብሔር አዘዘ በእደ ሙሴ ከመ የሀቡን ርስተነ በማዕከለ አኃዊነ ወወሀብዎን በትእዛዘ እግዚአብሔር ምስለ አኃዊሁ ለአቡሆን ፤

እነዚህም መጥተው በሊቀ ካህናቱ በአልዓዛርና በኢያሱ ፊት በእስራኤል አለቆችም ፊት ቆመው በወንድሞቻችን መካከል ርስታችንን ይሰጡን ዘንድ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል አዞልን ነበር አሉ ፤ በእግዚአብሔር ትእዛዝም ከአባታቸው ወንድሞች ጋር ርስታቸውን ሰጧቸው ፤

፭፤ ወወድቀ ሐብለ ምናሴ ፲ቱ እንበለ ገለዓድ ወባሳን ዘማዕዶተ ዮርዳኖስ ፤

በዮርዳኖስ ማዶ ካለው ከባሳንና ከገለዓድ በቀር የምናሴ ዕጣ ፲ሁኖ ወደቀ ፤

፮፤ እስመ አዋልደ ደቂቀ ምናሴ ተዋረሳ ርስተ በማዕከለ አኃዊሆን ወምድረ ገለዓድሰ ኮነት ለደቂቀ ምናሴ እለ ተርፉ ፤

የምናሴ ልጅ፣ የሰለጸዓድ ልጆች በወንድሞቻቸው መካከል ርስት ወርስዋልና ገለዓድ ግን ለቀሩት ለምናሴ ልጆች ሆነች ፤

፯፤ ወኮነ ደወሎሙ ለደቂቀ ምናሴ እምአሴራ ዴላናታ እንተ ቅድመ

ገጸሙ ለደቂቀ ሴኬም ወየሐውር
ኅዕለ ደወሎሙ ለኢያሚን በውስተ
ኢያቢስ ዲበ ነቅዓ ተፍቶት ፣

የምናሴ ልጆች ደንበር በሴኬም
ልጆች አንፃር (ፊት ለፊት)
ካለች ከአሴራ ዴላናታ ጀምሮ
በተፍቶች ባለች ምንጭ በኢያ
ቢስ በኩል ወደ ኢያሚን አው
ራጃ ይደርሳል ።

፰፤ ወኮነ ለምናሴ ጣፌት ፣ ወጣፌ
ትሰ ኀበ ደወሎሙ ለደቂቀ ምናሴ
ወለደቂቀ ኤፍሬም ፣

ጣፌት ለምናሴ ዕጣ ሆነ፣ ይኸው
ጣፌት ግን በኤፍሬም ልጆችና
በምናሴ ልጆች አውራጃ መካ
ከል ያለ ነው ።

፱፤ ወይወርድ ደወሎሙ ኅዕለ ቈላተ
ቃሬና ዘኀበ አዜብ ወዲበ ቈላተ
ኢያርያል ወጤሬምንቶን ዘኤፍሬም
ማዕከለ አህጉረ ምናሴ ወደወሉሂ
ለምናሴ ኅዕለ መስዕ እንተ ኀበ
ፈለግ ፣

ወሰናቸው በአዜብ በኩል ወደ
አለች ወደ ቃሬና ቈላና የኤፍ
ሬም ዕጣ ወደምትሆን ወደጤ
ሬምንቶንና ወደኢያርያል በረ
ሀም ይደርሳል፣ የምናሴም አው
ራጃ ወንዝ ባለበት በመስዕ (በሰ
ሜን) በኩል ነው ።

፲፤ ወኮነ ሞፃእቱ ባሕር እንተ መን
ገለ አዜቡ ለኤፍሬም ወዘኀበ መስዑ
ለምናሴ ወይከውን ባሕር ወሰኖሙ
ወበአሴር ይትራከቡ በመስዕ ወበይ
ሳኮር እምጽባሕ ፣

ፍጻሜውም በምናሴ ዕጣ ቀኝና
በኤፍሬም ዕጣ ግራ ያለ ባሕር
ነው፣ ወሰናቸውም ባሕር ነው፣
ከአሴር ጋር በቀኝ ይገናኛሉ ፣
ከይሳኮርም ጋር በምሥራቅ ይገ
ናኛሉ ።

፲፩፤ ወይከውን ለምናሴ በይሳኮር
ወበአሴር ቶሃን ወሙፋራቲሃ ወእለ
ይነብሩ ውስተ ዶር ወሙፋራቲሃ
ወእለ ይነብሩ ውስተ ጌዳ ወሙፋራ
ቲሃ ወሣልስተ እዴሃ ለመፌታ ወሙ
ፋራቲሃ ፣

በይሳኮርና በአሴር መካከል
ያለች ቶሃን ከመሰማሪያዋ ጋር
የምናሴ ዕጣ ሆነች ፣ በዶር
የሚኖሩ ሰዎች ከመሰማሪያዋ
ጋር ፣ በጌዳ የሚኖሩ ሰዎችም
ከመሰማሪያዋ ጋር የመፌታም
ሲሶዋ ከመሰማሪዋ ጋር ለምናሴ
ሆኑ ።

፲፪፤ ወስእኑ ደቂቀ ምናሴ አጥፍኦ
ቶን ለእላንቱ አህጉር ወመጽኡ ከና
ኔዎን ይንበሩ ውስተ ይእቲ ምድር ፣

የምናሴ ልጆች አሁን የተናገር
ናቸውን እነዚህን አገሮች ማጥ
ፋት ተሳናቸው ፣ ከናኔዎን የሚ
ባሉ አሕዛብም በዚያች አገር
ይኖሩ ዘንድ መጡ ።

፲፫፤ ወጸንዕዎሙ እስራኤል ወቀነይ
ዎሙ ወአጥፍኦ ባሕቱ ኢያጥፍእ
ዎሙ ፤

እስራኤል በርትተው ገዟቸው፣
ነገር ግን ፈጽመው አላጠፏቸ
ውም ፤

፲፬፤ ወተዋቀስዎ ደቂቀ ዮሴፍ ለኢ
ያሱ ወይቤልዎ በበይነ ምንት አው
ረስከነ ፩ደ ርስተ ወ፩ደ ሐብለ
እንዘ ብዙኀ ሕዝብ ንሕነ ወእግዚ
አብሔር ባረከነ ፤

የዮሴፍ ልጆች ኢያሱን እኛ ብዙ
ወገን ስንሆን እግዚአብሔር ሲያ
ከብረን ስለምን ፩ ዕጣ ፩ርስት
ብቻ አወረስከን ? ብለው ወቀ
ሱት ፤

፲፭፤ ወይቤሎሙ ዕርጉ ኀበ ኢያር
ምር ወአንጽሕዋ ለክሙ እመ ይጸብ
በክሙ ደብረ ኤፍሬም ፤

እሱም የኤፍሬም ዕጣ ከጠበባ
ችሁ ወደ ኢያርምር ወጥታችሁ
አቅኗት ፤ አንድም በርሷ ያሉ
አሕዛብን አጥፍታችሁ ውረሷት
አላቸው ፤

፲፮፤ ወይቤሉ ኢያአክለነ ደብረ ኤፍ
ሬም ወከናኔዎን እለ ይነብሩ ውስ
ቴቱ ቦሙ አፍራስ ኀሩያን ወሐፂን
በቤቴል ወበሙፋራቲሃ በቈላተ ኢይ
ዝራኤል ፤

እነሱም የኤፍሬም ዕጣ አይበ
ቃነም አሉ ፤ በዚያ የሚኖሩ የከ
ናኔዎን ወገኖች ብዙ የሆኑ ፈረ
ሶች አሏቸውና በኢይዝራኤል
ቈላ በመስማሪያዋና በቤቴልም
ጦር አላቸውና አይበቃንም
አሉ ፤

፲፯፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ
ዮሴፍ እስመ ብዙኀ ሕዝብ አንተ
ወብከ ዓቢይ ኃይል ኢይከውነከ ፩ዱ
ርስት ፤

ኢያሱም የዮሴፍን ልጆች እን
ዲህ አላቸው፣ አንተ ብዙ ወገን
ነህና ብዙ ሠራዊትም አለህና
፩ ዕጣ (ርስት) አይበቃህም ፤

፲፰፤ እስመ ደብር ለከ ውእቱ እስመ
ገዳም ውእቱ ወታነጽሖ ለከ ወይከ
ውነከ እስከ ታጠፍኦሙ ለከናኔዎን
እስመ ሠረገላ ሐፂን ሎሙ ወጽኑዕ
ውእቱ ወአፍራስ ኀሩያን ቦሙ ወለ
ሊከ ጸናዕካሆሙ ፤

ምድረ በዳ ስለሆነ አውራጃ
ቸው ለአንተ ይሁን፣ ለአንተም
ጉልት አድርገው የብረት ሠረ
ገላ አላቸውና ፤ ሠረገላውም
ጽኑዕ ነውና ፤ የተመረጡ ፈረ
ሶችም አሏቸውና፣ አንተም አጽ
ንተህ ገዝተሃቸዋልና የከናኔዎ
ንን ወገኖች እስክታጠፋቸው
ድረስ ለናንተ ይሁን አላቸው ።

## ምዕራፍ ፲፰

፩፤ ወተጋብኡ ኵሉ ተዓይኒሆሙ
ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ሴሎ ወተ

ክልዋ በህየ ለደብተራ መርጡል ወአጽንዕዋ ለምድር እሙንቱ ፣

የእስራኤል ልጆች ወገኖች ሁሉ በሴሎ ተሰብስበው ደብተራ ኦሪትን በዚያ ተከሏት ፣ እነሱም ከነዓንን አጽንተው ወረሷት ፤

፪፤ ወተርፉ ደቂቀ እስራኤል እለ ኢተዋረሱ ፯ቱ ነገድ ፣

ከእስራኤል ልጆች ርስት ያልወረሱ ፯ ነገድ ቀሩ ፤

፫፤ ወይቤሎሙ ኢያሱ ለደቂቀ እስራኤል እስከ ማእዜኑ ታጸንሕዋ ለምድር ዘወሀበክሙ እግዚአብሔር አምላክነ ከመ ኢትትዋረስዋ ፣

ኢያሱም የእስራኤልን ልጆች ፈጣሪያችን እግዚአብሔር የሰጣችሁን አገር እንዳትወርሷት እስከ መቼ ድረስ ታቆዩዋታላችሁ ? አንድም የምታቆዩዋት እስከ መቼ ድረስ ነው ?

፬፤ አውጽኡ እምውስቴትክሙ ፫ተ ዕደወ እምነገድ ውስተ ነገድ ወይትነሥኡ ይዑድዋ ለምድር ወይጽሐፍዋ ወይርአይዋ ወይምጽኡ ኀቤየ ወተካፈልዋ ፯ተ መክፈልተ ፣

ከየነገዳችሁም ፫ት ፫ት ሰው አውጡ ፣ ተነሥተውም አገሪቱን ዞረው ይቍጠሯት ፣ አይተዋትም ወደኔ ይምጡ ሰባት ዕጣም አድርጋችሁ ተካፈሏት አላቸው ፤

፭፤ ወአቀመ ሎቱ ይሁዳ ደወሎ መንገለ አዜብ ወደቂቀ ዮሴፍ አቀሙ ደወሎሙ መንገለ መስዕ ፣

ነገደ ይሁዳም ደንበሩን (አውራጃውን) በአዜብ (በግራ) አጸና፣ የዮሴፍም ልጆች ደንበራቸውን በመስዕ (በሰሜን) አጸኑ ፤

፮፤ ወአንትሙሰ ክፍልዋ ለምድር ፯ተ ክፍለ ወአምጽኡ ኀቤየ ዝየ ወአበውእ ለክሙ ርስተ ወአወጽእ ለክሙ ዝየ ዕፃ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክክሙ ፣

እናንተ ግን ምድሪቱን ሰባት ዕጣ አድርጋችሁ ክፈሏት፣ የተጻፈበትንም መዝገብ ወደኔ አምጡ ፣ እኔም ርስት አድርጌ እሰጣችኋለሁ ፣ በፈጣሪያችሁ በእግዚአብሔርም ፊት ዕጣ አጣጥላችኋለሁ ፤

፯፤ እስመ አልቦሙ ክፍል ለደቂቀ ሌዊ ምስሌክሙ እስመ ክህነቱ ለእግዚአብሔር ክፍሎሙ ፣

የእግዚአብሔር ክህነቱ ዕጣቸው ስለሆነ ፣ አንድም ደብተራ ኦሪትን ማገልገላቸው ዕጣቸው ስለሆነ የሌዊ ልጆች ከናንተ ጋራ ዕድል ፈንታ የላቸውምና እናንተን በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ አጣጥላችኋለሁ ፤

ወጋድስ ወሮቤል ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ ነሥኡ ርስቶሙ በማዕዶተ

ዮርዳኖስ ጽባሐዊ ዘወሀቦሙ ሙሴ ቀኅልዔሁ ለእግዚአብሔር ፤

የሮቤልና የጋድ ወገኖች የምናሴም ነገድ እኩሌታ ግን ከዮርዳኖስ ማዶ ወዲያ በምሥራቅ በኩል የእግዚአብሔር ባለሟል ሙሴ የሰጣቸውን አገር ርስት አድርገው ያዙ ፤

፰፤ ወተንሥኡ እሙንቱ ዕደው ወሖሩ ወአዘዞሙ ኢያሱ ለእለ የሐውሩ ይዑድዋ ለምድር ወይቤሎሙ ሖሩ ዑድዋ ለምድር ወጸሐፍዋ ወግብኡ ኀቤየ ዝየ ከመ አውጽእ ለክሙ ዕፃ ቅድመ እግዚአብሔር በሴሎ ፤

እነዚያም ሰዎች ተነሥተው ሔዱ ኢያሱም ምድርን ይጐበኟት ዘንድ የሚሔዱትን ሰዎች ሒዳችሁ አገሪቱን ዙራችሁ አይታችሁ ጽፋችሁ (ቈጥራችሁ) በሴሎ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ አጣጥላችሁ ዘንድ ወደኔ ተመለሱ ብሎ አዘዛቸው ፤

፱፤ ወሖሩ ወዖድዋ ለምድር ወርእይዋ ወጸሐፍዋ ውስተ መጽሐፍ በበአህጉሪሃ ወአምጽኡ ኀበ ኢያሱ ፤

እነሱም ሒደው አገሪቱን ዙረው አይተው በየአውራጃዋ ጽፈው ወደ ኢያሱ አመጡ ፤

፲፤ ወአብአ ኢያሱ መክፈልቶሙ ቅድመ እግዚአብሔር በሴሎ ፤

ኢያሱም በሴሎ በእግዚአብሔር ፊት ዕጣ አጣጣላቸው ፤

፲፩፤ ወበጽሐ ክፍሉ ለብንያም ቅድመ በበሕዘቢሆሙ ወረከቦሙ ደወለ መክፈልቶሙ ማእከለ ደቂቀ ይሁዳ ወማእከለ ደቂቀ ዮሴፍ ፤

የነገደ ብንያም ዕጣ አስቀድሞ ወጣ ፤ ዕድል ፈንታቸው በይሁዳ ልጆችና በዮሴፍ ልጆች ዕጣ መካከል ደረሳቸው ፤

፲፪፤ ወኮነ ደወሎሙ ዘመንገለ ሰሜን እምዮርዳኖስ ወየዐርግ ላዕለ አዜባ ለኢያሪኮ እምሰሜን ወየዐርግ ላዕለ ደብር ዘነበ ባሕር ወይከውን ሞፃዕቱ ምድብራይጣስ ዘቤቶን ፤

አውራጃቸውም ከዮርዳኖስ በሰሜን በኩል ሆነ ከሰሜንም ጀምሮ ወደ ኢያሪኮ ደቡብ (ግራ) ይደርሳል፤ ከዚያውም ዘንድ በባሕር አጠገብ ወዳለው ተራራ ይደርሳል፤ መጨረሻውም የቤቶን ዕጣ የሚሆን ምድብራይጣስ ነው ፤

፲፫፤ ወዮነልፍ እምህየ ላዕለ አድባረ ሎዛ እንተ ዘባነ ሎዛ እንተ ዲበ አዜብ እንተ ይእቲ ቤቴል ወይወርድ ላዕለ ደወለ አጣሮት ዘሆሬህ እንተ ላዕለ አድባር ዘመንገለ አዜባ ለቤቶሮን ታሕታይ ፤

ከዚያም ይችውም ቤቴል ናት፤ በአዜብ በኩል ካለች ከሎዛ በላይ እስካለው እስከ ሎዛ ተራራ ይደርሳል፤ በታችኛው ቤቶሮን በስተግራ ባለው ተራራ አድርጎ የሆሬህ ዕጣ ወደምትሆን ወደ አጣሮትም ይወርዳል ፤

፲፬፡ ወዮነልፍ ላዕለ ፩ ኅብር ዘይኔጽር መንገለ ባሕር ዘመንገለ አዜቡ ለደብር ዘቅድመ ቤቶሮን ዘቅድመ አዜባ ፡

በአዜብ አንፃር ባለ በቤቶሮን ፊት ለፊት በተራራው በስተግራ ወዳለው ባሕር ወደሚወስድ ወደ አንድ ወገኑ ይደርሳል ፡

ወይከውን ሞፃዕቱ ላዕለ ቀርያትበዓል እንተ ይእቲ ቀርያታርም ሀገረ ደቂቀ ይሁዳ ወዝንቱ ውእቱ ደወሎሙ ዘመንገለ ባሕር ፡

ይኸውም የይሁዳ ልጆች አገር ቀርያታርም ናት ፡ ፍጻሜው ቀርያትበዓል ነው ፡ በባሕሩ በኩል ደንበራቸው ይህ ነው ፡

፲፭፡ ወደወሎሙኒ ዘመንገለ አዜብ እምቀርያትበዓል ወዮነልፍ ላዕለ ጋይን ዲበ ነቅዓ ማይ ዘነፍቶ ፡

ከቀርያትበዓልም በአዜብ (በደቡብ) በኩል ያለ አውራጃቸው ነፍቶ በሚባል አገር ባለ የውሃ ምንጭ አድርጎ ወደጋይን ይደርሳል ፡

፲፮፡ ወይወርድ ላዕለ ፩ ኅብር ዘቅድመ ናጺስናም ዘመንገለ ገቦሃ ለኢማቅርፋይን ዘነበ መስዕ ፡

በሰሜን በኩል ወዳለች በማቅርፋይን ጐን በናጺስናም ፊት ለፊት ወዳለ ወዳንድ ወገን ይወርዳል ፡

ወይወርድ እምናጺን ዲበ ዘባነ ኢያቡሴ ዘነበ አዜብ ወይወርድ ዲበ ነቅዓ ሮጌል ፡

ከናጺንም በደቡብ አጠገብ ወዳለ ወደ ኢያቡሴ ይወርዳል ፡ ወደ ሮጌል ምንጭም ይወርዳል ፡ ሐተታ ነቅዓ ሮጌል እንዲል እንድኪ የሚያገቡበት በፍታ የሚያፋጥቁበት ቀለም የሚያገቡበት ምንጭ ነው ፡

፲፯፡ ወዮነልፍ ዲበ ነቅዓ ቤተ ሳሚስ ወይበውእ ዲበ ከልዮት እንተ ቅድመ አቀበ ኢታምን ወይወርድ ዲበ ዕብነ ቤዜዎን ዘደቂቀ ሮቤል ወዮነልፍ ዲበ ዘባነ ቤተ ራባ ዘነበ መስዕ ፡

ከዚያም በሳሚስ ቤት አጠገብ ወዳለው ምንጭ ይደርሳል ፡ በኢታምን ዓቀበት ፊት ለፊት ወዳለ ወደ ከልዮትም ይገባል ፡ የሮቤል ልጆች ዕጣ ወደሚሆን ወደቤዜዎን ደንጊያ ይደርሳል ፡ በመስዕ በኩል ወዳለ ወደ ቤተ ራባ አጠገብም ይደርሳል ፡

፲፰፡ ወይወርድ ላዕለ ፍኖተ ባሕር ዘመንገለ መስዕ ፡

በመስዕ (በሰሜን) በኩል ወደ ባሕሩ ወደሚወስደው መንገድ ይደርሳል ፡

፲፱፡ ወይከውን ሞፃዕቱ ለደወሎሙ ላዕለ ፍኖተ ባሕር ዘአሉን መንገለ

መስዕ ወዝብሁ ለዮርዳኖስ ዘንበ አዜብ ዝንቱ ደወለ አዜብ ፤

የደንበራቸውም ፍጻሜ በሰሜን በኩል ባለ በአሎን ባሕር መን ገድ ይደርሳል፣ በአዜብም በኩል ደንበራቸው ዮርዳኖስ ነው ፤

፳፤ ወዮርዳኖስ ወሰኖሙ መንገለ ጽባሕ ወዝንቱ ውእቱ ደወሎሙ ዘዓ ውደሙ ለደቂቀ ብንያም በበሕዘቢሆሙ ዘተዋረሱ ፤

በምሥራቅም በኩል ደንበራቸው ዮርዳኖስ ነው፣ በየወገናቸው የወ ረሱት የብንያም ልጆች አውራ ጃቸው ይህ ነው ፤

፳፩፤ ፳፪፤ ወኮና አህጉሪሆሙ ለደ ቂቀ ብንያም በበሕዘቢሆሙ ዘተዋ ረሱ ኢያሪኮ ወቤተግዎ ወአመቀ ሰስ ወቤተበራ ወሠአርቃ ቤፋና ፤

የብንያም ልጆች በየወገናቸው የወረሷቸው አገሮቻቸው ኢያ ሪኮና ቤተግዎ፣ ቤተበራና አመ ቀሰስ፣ ሰአርቃና ቤፋና ናቸው ፤

፳፫፤ ፳፬፤ ወአይን ወፋራ ወኤፍ ራታ ወቃራፋ ወቂፋራ ሞዓ ወጉባሕ አሥሩ ወክልኤቲ አህጉር ወሙፋራ ቲሆን ፤

አይንና ፋራ ፣ ኤፍራታና ቃራፋ፣ ቂፋራና ሞዓ ጉባሕም ከመሰማሪያቸው ጋራ እነዚህ አሥራ ሁለቱ አገሮች ናቸው ፤

፳፭፤ ገባዖን ወራማ ወማሴማ ወቤ ሮን ወሞቄ ወቤራ ፤

ገባዖንና ራማ ማሴማና ቤሮን ሞቄና ቤራ ፤

፳፮፤ ወቃፋን ወቃና ወሴሌቃን ወቴ ርስላ ፤

ቃፋንና ቃና ሴሌቃንና ቴር ስላ ፤

፳፯፤ ወኢያቡሴዎን እንተ ይእቲ ኢየሩሳሌም ወገባዖን ወሀገረ ኢያ ሪን አሥሩ ወሠለስ አህጉር ወሙ ፋራቲሆን ፤

ይችውም ኢየሩሳሌም ናት ፣ ኢያቡሴዎንና ገባዖን የኢያሪ ንም አገር ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር እነዚህ አሥራ ሦስቱ አገ ሮች ናቸው ፤

፳፰፤ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለደ ቂቀ ብንያም በበሕዘቢሆሙ ፤

በየወገናቸው የብንያም ልጆች የወረሱት ርስታቸው ይህ ነው ።

## ምዕራፍ ፲፱

፩፤ ወበጽሐሙ ለደቂቀ ስምዖን ካልዕ ክፍል ወኮነ ርስቶሙ ውስተ ማዕከ ሎሙ ለደቂቀ ይሁዳ ፤

ለስምዖን ልጆች ሁለተኛ ዕጣ ደረሳቸው፣ ርስታቸውም በይ ሁዳ ልጆች ርስት መካከል ነው ፤

፪፡፫፡ ወረከቦሙ፡ መክፈልቶሙ፡ ቤር ሳቤህ ወሰማህ ወቆሎንዶን ወአርሳባ ወባላ ወኢያሶን ፤

ዕጣቸው ቤርሳቤህና ሰማህ ፤ ቆሎንዶንና አርሳባ ባላና ኢያሶን ናቸው ፡፡

፬፡፭፡ ወልዑላ ወቡል ወኤርማ ወሴቄላቅ ወቤተማክሬብ ወሶርሶኢን ወአቦታሩት ፤

ልዑላና ቡል ኤርማ እና ሴቄላቅ ቤተ ማክሬብ እና ሶርሶኢን አቦታሩትም ናቸው ፡፡

፮፡ አሥሩ ወሠላስ አህጉር ወሙፋራቲሆን ፤

እስከ አሥራ ሦስቱ አገሮች ሁሉ ከመሰማሪያቸው ጋር ዕድል ፈንታቸው ሆኑ ፡፡

፯፡ ሬሞን ወቴልካ ወኢያቴር ወአሣ አርባዕ አህጉር ወሙፋራቲሆን ዘአውዶን ለእላንቱ አህጉር እስከ ባሌቅ ፤

ሬሞንና ቴልካ ኢያቴርና አሣ እስከ ባሌቅ ድረስ በነዚህ አገሮች ዙሪያ ካሉ ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር አራቱ አገሮችም ደረሷቸው ፡፡

፰፡ ወየኀልፍ ላዕለ ባሚት ዘመንገለ አዜብ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ስምዖን ፤

በአዜብ በኩል (በግራ በኩል) ወደባሚት ይደርሳል፤ የስምዖን ልጆች ነገደ ርስታቸው ይህ ነው ፡፡

፱፡ እስመ ኮነ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ይሁዳ ዓቢየ እምዚአሆሙ ወወረሱ ደቂቀ ስምዖን ማዕከለ መክፈልቶሙ ፤

የይሁዳ ልጆች ዕጣ ከነሱ ዕጣ ከፍ ያለ ሁኗል እና የስምዖን ልጆች በነሱ ዕጣ መካከል ርስት ወረሱ ፡፡

፲፡ ወረከቦሙ ሣልስ መክፈልት ለደቂቀ ዛብሎን በበሕዘቢሆሙ ወኮነ ደወለ ርስቶሙ ኤሴዴቅ ወኀላ እምባሕር ወመግሬላ ፤

ለዛብሎንም ልጆች በየወገናቸው ሦስተኛ ዕጣ ደረሳቸው ፤ የርስታቸውም ደንበር ኤሴዴቅና ኀላ በምዕራብ በኩል ያለ መግሬላ ነው ፡፡

፲፩፡ ወይትአኀዝ ምስለ ቤተ ራባ ዘውስተ ቄላት እንተ ቅድመ ገጸ ለኢያቃምን ፤

በኢያቃምን አንፃር ባለ ቄላ ካለች ከቤተ ራባ ጋር ይገናኛል (የተያያዘ ነው) ፡፡

፲፪፡ ወተመይጠ እምሳዴቅ ላዕለ ቅድመ ጽባሒሁ ለቤተ ሳሚስ ዳበ ደወለ አካሲሎቴት ፤

ከሳዴቅ አንሥቶ በሳሚስ ቤት ምሥራቅ አንፃር ወደአካሲሎቴት ዳርቻ ይመለሳል ፡፡

፲፫፡ ወየኀልፍ እንተ ዳቤሮት ወየዐርግ ላዕለ ፌጢ ወየኀልፍ ዘቅድመ ጽባሒሁ ለሀገረ ጌቤሮ እንተ ኀበ

ሴም ወየኀልፍ ዲበ ሬሞን ዘአም
ተርዮዛ ።

ወደ ዳቤሮት ይደርሳል ። ወደ ፌጢም ይወጣል ። በሴም ዕጣ ወዳለ ወደ ጌቤር አገር ምሥራቅም ይደርሳል ፤ የዘአምተርዮዛ ዕጣ ወደምትሆን ወደ ሬሞንም ያልፋል ፤

፲፬፡ ወየኀልፍ ሳዕለ መስዓሞት ወይከውን ሞፃዕቶሙ ሳዕለ ጌፋሄል እንተ ኀበናት ።

ወደ መስአሞትም ይደርሳል ። ፍጻሜውም በኀበናት በኩል ያለ ጌፋሄል ነው ፤

፲፭፡ ወናበሀል ወሲሞዖን ወዲኤል ወሜቴሜን አሥሩ ወክልኤ አህጉር ወሙፋራቲሆን ።

ናበሀልና ሲሞዖን ዲኤልና ሜቴሜን እሊህ አሥራ ሁለቱ አገሮች ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር ዕድል ፈንታ ሆናቸው ፤

፲፮፡ ዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ዛብሎን በበሕዘቢሆሙ እለ አህጉር ወሙፋራቲሆን ።

የዛብሎን ልጆች በየወገናቸው የወረሷቸው አገሮች ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር እሊህ ናቸው ፤

፲፯፡ ወረከበሙ ለደቂቀ ይሳኮር ራብዕ መክፈልት ።

ለይሳኮርም ልጆች አራተኛ ዕጣ ደረሳቸው ፤

፲፰፡ ወኮነ ደወሎሙ ኢይዝራኤል ወካልስሎት ወሱሳን ።

አውራጃዎቻቸውም ኢይዝራኤልና ካልስሎት ሱሳን ናቸው ፤

፲፱፡ ፳፡ ወአጊን ወሴዎናን ወርሄቱ ወአንክሬት ወዳቤራት ወቂሶን ወሮቤስ ወሬማን ወኤግፌቅ ወቤርሳቤሕ ።

አጊንና ሴዎናን፣ ርሄቱና አንክሬት ፣ ዳቤራት እና ቂሶን ፣ ሮቤስና ሬማን ኤግፌቅና ቤርሳቤሕም ናቸው ፤

፳፩፡ ወይትአኀዝ ደወሎሙ ለታቦር ወሳዕለ ሳሌም እንተ መንገለ ባሕር ወቤተ ሳሚስ ።

ደንበራቸውም በታቦርና በባሕር አንፃር ባለች በሳሌም በቤተሳሚስም ይያያዛል (ይገናኛል) ፤

፳፪፡ ወይከውን ሞፃዕተ ደወሎሙ ዮርዳኖስ አሥሩ ወስሱ አህጉር ወሙፋራቲሆን ።

የደንበራቸውም ፍጻሜ ዮርዳኖስ ነው እነዚህ አሥራ ስድስቱ አገሮች ሁሉ ከመሰማሪያዎቻቸው ጋራ ደረሷቸው ፤

፳፫፡ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ ይሳኮር በበሕዘቢሆሙ ወአህጉሪሆሙኒ ወአዕፃዲሆሙ ።

የይሳኮር ልጆችም በየወገናቸው የወረሱት ርስታቸውና አገራቸው አውራጃቸውም ይህ ነው ፤

፳፬፤ ወረከቦሙ ኃምስ መክፈልት ለደቂቀ አሴር ፣

ለአሴርም ልጆች አምስተኛ ዕጣ ደረሳቸው ፤

፳፭፤ ወኮነ ደወሎሙ እምኤልኬት ወኤሌፍ ወቤቶቅ ወአቂያፋ ወአሊሚሊ ወአሚሔል ወማሕሳ ፣

አውራጃዎቻቸውም ከኤሌኬትና ከኤሌፍ ከቤቶቅና ከአቂያፋ ከአሌሜሊና ከአሜሂል ከማሕሳም ጀምሮ ነው ፤

፳፮፤ ወይትአነዝ በቀርሜሎስ ዘመንገለ ባሕር ወበሲዎን ወለበንት እምጽባሒሁ ወይገብእ በቴጌኔት ፣

በምዕራብ በኩል ባለ በቀርሜሎስና በሲዎን ይገኛል፣ ከምሥራቅም በኩል ከለበንት ጋር ይገናኛል፣ ወደ ጌቴኔትም ይደርሳል፤

፳፯፤ ወይትአነዝ በዛብሎን ወእምጌጊ ወፍትሔል ዘመንገለ መስዕ ወይበውእ ደወሎሙ ውስተ ሳፍቱ ቤታሜህ ወኤንሔል ወዮነልፍ ውስተ ኮበም ወአሲሜል ፣

በሰሜን በኩል ካሉ ከፍትሔልና ከጌጊ ጀምሮ ከዛብሎን ጋር ይገናኛል ፣ ወሰናቸውም ወደ ሳፍቱና ቤታሜህ ፣ ወደ ኤንሔልም ይገባል ፣ ወደ ኮበምና ወደ አሲሜልም ይደርሳል ፤

፳፰፤ ወኬብሮን ወረዓብ ወኤሜማህን ወቀንታኔዎን እስከ ሲዶና ዓቢይ ፣

ወደ ኬብሮንና ወደ ረዓብ ወደ ኤሜማህንና ወደ ቀንታኔዎን ሰፊ እስከሆነ እስከ ሲዶናም ይደርሳል ፤

፳፱፤ ወይገብእ ደወሎሙ ውስተ ዓራማ ወእስከ ሀገረ ቅጽረ ጢሮስ ወይገብእ ደወሎሙ ውስተ ኢያሳፍ ወይከውን ደወለ ሞፃዕቱ ባሕር እምኒሌብ ወኮዛብ ፣

አውራጃቸውም ወደ አራማ ይደርሳል ፣ እስከ ጢሮስ ቅጽር አንባም ይደርሳል ደንበራቸውም ወደ ኢያሳፍ ይመለሳል ፣ የፍጻሜውም ደንበር ከሌብና ከኮዛብ አጠገብ ያለ ባሕር ነው ፤

፴፤ ወአርኮብ ወአፌቅ ወረአው ፳ወ፪ኤ አህጉር ወሙፋሪቲሆን ፣

አርኮብና አፌቅ ረአው እኒህ ሃያ ሁለቱ አገሮች ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር ዕድል ፈንታቸው ሆኑ ፤

፴፩፤ ዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ደቂቀ አሴር በበሕዘቢሆሙ ወአህጉሪሆሙኒ ወሙፋሪቲሆሙ ፣

የአሴር ልጆች በየወገናቸው የወረሱት ርስታቸውና አገራቸው መሰማሪያቸውም ይህ ነው ፤

፴፪፤ ወረከቦሙ ለደቂቀ ንፍታሌም
ሳድስ ክፍል ፤

ለንፍታሌም ልጆች ፮ኛ ዕጣ
ደረሳቸው ፤

፴፫፤ ወኮነ ደወሎሙ መሐላም ወሞላ
ወቤሴሜዩን ወአርሚ ወኖባ ወኢያ
ፍታሜን እስከ አእዳላን ወኮነ ሞፃ
ዕቱ ዮርዳኖስ ፤

አውራጃቸውም መሐላምና ሞላ
ቤሴሜዩንና አርሚ ኖባና ኢያ
ፍታሜን እስከ አእዳላን ድረስ
እነዚህ ናቸው ፤ ፍጻሜውም
ዮርዳኖስ ነው ፤

፴፬፤ ወይገብእ ደወሎሙ ላዕለ ባሕረ
አናብትሮን ወየኀልፍ እምህየ ላዕለ
አቃናቃ ወይትአኀዝ በዛብሎን እመ
ንገለ አዜብ ወአሴርሂ ይትአኀዝ
መንገለ ባሕር ወበይሁዳ ወዮርዳኖስ
እመንገለ ጽባሕ ፤

ወሰናቸውም በአናብትሮን ባሕር
ይገባል ፤ ከዚያም በአቃናቃ
ላይ ያልፋል ፤ በደቡብ በኩል
ከዛብሎን በምዕራብ በኩልም
ከአሴርና ከይሁዳ ዕጣ ይገና
ኛል ፤ በምሥራቅም በኩል ከዮ
ርዳኖስ ይደርሳል ፤

፴፭፡፴፮፤ ወአህጉረ ሲዶና እለ ቅጽር
ቦን ወጢሮስ ወእምዴቄቅ ወቄሬት
ወአርሜት ወአራሂን ወአሦር ወቃ
ዴስ ወአስራዶስ ወነቅዓ አሦር ፤

ቅጥር ያላቸው የሲዶና አገሮ
ችም ጢሮስና እምዴቄቅ ቄሬ
ትና አርሜት አራሂንና አሦር
ቃዴስ እና አስራዶስ የአሦርም
ምንጭ ናቸው ፤

፴፯፡፴፰፤ ወቆሬ ወሚጋላህሮም ወቤ
ታሚ ወታስሜሲ አሥሩ ወተስዑ
አህጉር ወሙፋራቲሆን ፤

ቆሬና ሚጋላህ ሮም ቤታሚና
ታስሜሲ ከመሰማሪያቸው ጋር
እነኚህ አሥራ ዘጠኙ አገሮች
ናቸው ፤

፴፱፤ ወዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነ
ገደ ደቂቀ ንፍታሌም ፤

የንፍታሌም ልጆች የወረሱት
ርስታቸው ይህ ነው ፤

፵፤ ወረከቦሙ ለደቂቀ ዳን ሳብዕ
ክፍል ፤

ለዳን ልጆችም ፯ኛ ዕጣ ደረሳ
ቸው ፤

፵፩፡፵፪፤ ወኮነ ደወሎሙ ሰራህት
ወአሳ ሀገረ ሰማውስ ወሰላቤን ወአ
ሞን ወሴላታ ፤

አውራጃቸውም ሰራህትና የሰማ
ውስ አገር አሳ፣ ሰላቤንና አሞን
ሴላታም ናቸው ፤

፵፫፡፵፬፤ ወኤቤን ወቴምናታ ወአ
ቃሮን ወለተቃታ ወጌቤቶን ወጌቤ
ሌን ፤

ኤቤንና ቴምናታ ፤ አቃሮንና
ለተቃታ ፤ ጌቤቶንና ጌቤሌን
ናቸው ፤

፵፰፥፵፮፥ ወአዘዞር ወቤኔቤዋቅ ወጌቱሬም ወእምባሕረ ኢያላቅን ደወል ዘቅሩብ ኢዮጴ ፤

አዘዞርና ቤኔቤዋቅ ጌቱሬም የኢዮጴ አቅራቢያ አውራጃ ከሚሆን ከኢያላቅን ባሕር ጀምሮ ይህ ሁሉ አገራቸው (ዕድል ፈንታቸው) ሆነ ፤

፵፯፥ ዝንቱ ውእቱ ርስቶሙ ለነገደ ዳን በበሕዘቢሆሙ ወአህጉሪሆሙኒ ወሙፋራቂሆሙ ፤

የዳን ልጆች (ወገኖች) በየወገናቸው የወረሱት ርስታቸውና አገራቸው መሰማሪያቸውም ይህ ነው ፤

ወኢያጥወቅዎሙ ደቂቀ ዳን ለአሞሬዎን እለ ያጠውቅዎሙ በውስተ ደብር ወኢያበውኅዎሙ አሞሬዎን ይረዱ ውስተ ቈላት ወነሥኡ እምኔሆሙ ፩ደ ኅብረ እምደወለ መክፈልቶሙ ፤

የዳን ልጆች በደጋ የሚያስጨንቋቸው አሞሬዎንን በቈላ፣ በቈላ የሚያስጨንቋቸውን ደግሞ በደጋ አላስጨነቋቸውም፣ ወደ ቈላውም ይወርዱ ዘንድ የዳንን ልጆች የአሞሬዎን ወገኖች አላሰናበቷቸውም (አላስለጠኗቸውም) ፤ ከነገደ ዳን አውራጃም አንዱን ወገን ያዙ ፤

፵፰፥ ወሖሩ ደቂቀ ዳን ወቀተልዎሙ ለለኪሶ ወነሥኡ ሀገሮሙ ወቀተልዋ በአፈ ሐጺን ወነበሩ ውስቴታ ወሰመዩ ስማ ዳን በስመ ዳን አቡሆሙ ፤

የዳን ልጆች ሒደው ለኪሶ የሚባሉ አሕዛብን ወግተው አገራቸውን እጅ አደረጉ ፤ በጦር ወግተውም በውስጧ ተቀመጡ ፤ ስሟንም በአባታቸው በዳን ስም ዳን ብለው ጠሯት ፤

ወቆሙ አሞሬዎን ከመ ይንበሩ ውስተ ኤዶም ወውስተ ላሚን ወጸንአት እዴሁ ለኤፍሬም ላዕሌሆሙ ወኮንዎሙ መጸብሐ ፤

የአሞሬዎን ወገኖችም በኤዶምና በላሚን ይኖሩ ዘንድ በጠላትነት ተነሱ ፤ ነገር ግን የነገደ ኤፍሬም ሥልጣን በነሱ ላይ ጸናች ፤ እነዚህም ለእስራኤል ገባር ሆኑ ፤

፵፱፥ ወሖሩ ይዑድዋ ለምድር በውስተ ደወሎሙ ወወሀብዎ ደቂቀ እስራኤል ክፍሎ ለኢያሱ በውስቴቶሙ በትእዛዘ እግዚአብሔር ፤

በየአውራጃቸው አገራቱን ዙረው አይዋት (ጎበኟት)፤ የእስራኤል ልጆችም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለኢያሱ በውስጣቸው ዕድል ፈንታውን ሰጡት ፤

፶፥ ወወሀብዎ ሀገረ ዘሰአለ ቴምናሳራህ ዘውስተ ደብረ ኤፍሬም ወነደቃ ለይእቲ ሀገር ወነበረ ውስቴታ ፤

በኤፍሬም ዕጣ ውስጥ የምትሆን የለመነውን ሀገር ቴምና

ሳራህን ሰጡት ፤ ያችንም ሀገር ቀጽሮ (ከተማ አድርጎ) በው ስጧ ኖረ ፤

፶፩፤ ወዝንቱ ውእቱ አክፋሊሆሙ ዘከመ አስተዋረስዎሙ አልዓዛር ካህን ወኢያሱ ወልደ ነዌ ወመላእክተ አበዊሆሙ ለነገደ እስራኤል በበመ ክፈልቶሙ በሴሎ በቅድመ እግዚ አብሔር በኀበ ኆኅተ ደብተራ ዘመ ርጡል ወፈጸሙ ክፊለ ምድር ፤

ካህኑ አልዓዛርና የነዌ ልጅ ኢያሱ የእስራኤል የነገዶቻቸው አለቆችም በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሴሎ በደብተራ ኦሪት ደጅ ሁነው ምድረ ርስትን በየፈንታቸው እንዳወረሷቸው (እንደ አካፈሏ ቸው) አከፋፈላቸው ይህ ነው ፤ እንዲህም አድርገው ምድሪቱን (አገሪቱን) ከፍለው ጨረሱ ፤ ሐተታ አገሩን ስለ ምን ተር ትሮ ቆጠረ ቢሉ አገሩን ዙሮ ፤ ድንበሩን ኮልኵሎ ማወቅ ይገባ ልና፤ አንድም ይህ የእገሌ ነው፤ ይህ የእገሌ ነው ብሎ ባይጽፍ ልጆቻቸው በተጣሉ ነበርና ፤ አንድም ጌታ ለአብርሃም ከነዓ ንን አወርስሃለሁ ብሎት ነበርና፤ ጌታ የተናገረውን እንዳላስቀረ ለማጠየቅ ተርትሮ ቆጠረ ።

## ምዕራፍ ፳

፩፤ ወነበቦ እግዚአብሔር ለኢያሱ ወይቤሎ ፤

እግዚአብሐሔርም ለኢያሱ እን ዲህ ብሎ ተናገረው ፤

፪፤ ንግሮሙ ለደቂቀ እስራኤል መበ ሎሙ ሀቡ አህጉረ ምስካይ ዘእቤለ ክሙ በእደ ሙሴ ፤

በሙሴ ቃል የነገርኳችሁን የመ ማጠኛ አገሮችን ስጡ ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው ፤

፫፤ ከመ ይስኪ ህየ ቀታሊ ዘቀተለ ነፍሰ በኢያእምሮ እንዘ ኢይፈቅድ ፤

ሳይወድ (እገላለሁ ሳይል) ነፍስ የገደለ ሰው በዚያ ይማጠን ዘንድ ፤

፬፤ ወግበሩ ለክሙ አህጉረ ምስካይ ወይ ስኪ ውስተ አሐቲ እምእላንቱ አህጉር ፤

ለእናንተ የመማጠኛ አገሮችን ሥሩ ነፍስ የገደለው ሰው ከነ ዚያ አገሮች በአንዲቱ ሀገር ይማፀን ፤

ወይቁም ውስተ ኆኅተ አንቀጸ ሀገር ወይንግሮሙ ቃሎ ለሊቃናተ ይእቲ ሀገር ወያበውእዎ ሰብአ ይእቲ ሀገር ኀቤሆሙ ወየሀብዎ መካነ ወይንበር ምስሌሆሙ ፤

ያም ሰው በከተማው በር ቁሞ ነገሩን ለዚያች አገር ሽማግሎች

ይንገሩቸው ፣ የዚያች አገር ሰዎችም ወደ እነሱ አግብተው ቦታ ይስጡትና ከነሱ ጋራ ይኑር ፤

፭፤ ወሶበ ዴገኖ አበ ደም ኢያግብእዎ ሎቱ ውስተ እዴሁ እስመ በኢያእምሮ ቀተሎ ለካልኡ ወእንዘ ኢይጸልኦ ቀዲሙ ፣

ባለ ደሙም ተከትሎት ቢመጣ ቀድሞ ጠብ ሳይኖረው ባለማወቅ ባልንጀራውን ገድሎታልና ፤ አንድም የገደለው ባለማወቅ ነውና አሳልፈው ለሱ በእጁ አይስጡት ፤

፮፤ ወይንበር ውስተ ይእቲ ሀገር እስከ ይበጽሕ ቅድመ ዓውድ ይትሐተት ወእስከ አመይመውት ካህን ዓቢይ ዘሀለወ በውእቱ መዋዕል ፣

ይመረመር ዘንድ ወደ አደባባይ እስኪደርስ በዚያ ወራት የተሾመው ሊቀ ካህናቱም እስኪሞት ድረስ በዚያች አገር ይኑር ፤

ወይእተ አሚረ ይገብእ ቀታሊ ወየአቱ ሀገሮ ውስተ ቤቱ ወውስተ ሀገር እንተ እምሀየ ሰከየ ወኢይቀትሎ አበደም ለቀታሊ እስከ ይቀውም ቅድመ ዓውድ ወይትሐተት ፣

ነፍስ የገደለ ሰው ያን ጊዜ ከተማጠነበት ቦታ ወደ ሀገሩና ወደ ቤቱ ይመለስ በአደባባይ ቆሞ እስኪመረመር ድረስም ያን ነፍስ ገዳይ ባለደሙ አይግደለው ፤

፯፤ ወፈለጥዎ ለቃዴስ በውስተ ገሊላ በውስተ ደብረ ንፍታሌም ወለሴኬም በውስተ ደብረ ኤፍሬም ወለሀገረ አርቦቅ እንተ ይእቲ ኬብሮን በደብረ ይሁዳ ፣

ከነገደ ንፍታሌም ዕጣ በገሊላ ውስጥ ያለ ቃዴስን ለይተው ሀገረ ምስካይ አደረጉት ፣ ከነገደ ኤፍሬም ዕጣ የምትሆን ሴኬምንም ሀገረ ምስካይ አደረጉ ፣ ከነገደ ይሁዳ ዕጣ የምትሆን ኬብሮን የተባለች አርቦቅንም ሀገረ ምስካይ (የመማጠኛ አገር) አደረጉ ፤

፰፤ ወበማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመንገለ ኢያሪኮ እመንገለ ጽባሕ ወሀቡ ባሦርሃ በሐቅለ ገጻም እምነገደ ሮቤል ወኤርሞት በገለዓድ እምነገደ ጋድ ወጋውሎን በባሳን እምነገደ ምናሴ ፣

በምሥራቅ በኩል በኢያሪኮ አንፃር ባለ በዮርዳኖስ ማዶም ከሮቤል ነገድ ዕጣ በምድረ በዳ ያለች ባሦርን ሰጡ፣ ከነገደ ጋድ ዕጣም በገለዓድ ያለች ኤርሞትን ሰጡ፣ ከነገደ ምናሴም በባሳን ያለች ጋውሎንን ሰጡ ፤

፱፤ እላንቱ ዘነረዩ እምነገደ እስራኤል ወለግዩርኒ ዘሀለወ ውስቴቶሙ ከመ ይስኪ ህየ ቀታሊ ኵሉ ዘቀተለ ነፍስ ሰብእ በኢያእምሮ ከመ

ኢይቅትሎ አበ ደም እስከ ይቀውም ቅድመ ዓውድ ወይትሐተት ፤

ከእስራኤል ነገድ ዕጣ የመረጧቸው መማጠኛዎች እነዚህ ናቸው ፤ ባለማወቅ የሰው ነፍስ የገደለ ሁሉ በአደባባይ ቁሞ እስኪመረመር ድረስ ባለደሙ እንዳይገድለው፤ በዚያ ይማጠን ዘንድ በውስጣቸው ለሚኖር ለመጻተኛውም መማጠኛ ሡሩ፤ ሐተታ ይህም ለጊዜው ተደርጓል ለኋላው ግን ምሳሌ ነው ፤ ሀገረ ምስካይ የእደ እግዚአብሔር ፤ በዚያ የሚኖሩት ከሥቃየ ገሃነም በእደ እግዚአብሔር ተጠብቀው የኖሩ የጻድቃን ምሳሌ ፤ «ነፍሰሙሰ ለጻድቃን ውስተ እደ እግዚአብሔር ወኢለከፎሙ ሥቃየ ገሃነም» እንዲል፤ በአፍአ ቢያገኘው ይግደለው አለ ፤ ከእደ እግዚአብሔር በአፍአ ያሉትን ሥቃየ ገሃነም የማግኘቱ፤ ሊቀ ካህናቱ የጌታ ምሳሌ ነው ፤ ሊቀ ካህናቱ እስኪሞት ድረስ ከሀገረ ምስካይ አይውጣ አለ ፤ ጌታ ሰው ሁኖ እስኪሞት ድረስ በእደ እግዚአብሔር ለመጠበቃቸው ምሳሌ፤ ሊቀ ካህናቱ ከሞተ በኋላ ግን ወደ ሀገሩ ይመለስ አለ ፤ ጌታ ከሞተ በኋላ ገነት መንግሥተ ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ ::

## ምዕራፍ ፳፩

፩፤ ወመጽኡ መላእክቲሆሙ ለደቂቀ ሌዊ ኀበ አልዓዛር ካህን ውኀበ ኢያሱ ወልደ ነዌ ውኀበ መላእክተ ነገደ አብያተ አበዊሆሙ ለሕዝበ እስራኤል በሴሎ በምድረ ከነዓን ፤

የሌዊ ልጆች አለቆችም ከካህኑ ከአልዓዛርና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ ከእስራኤል ወገኖች የቤት አለቆችም ዘንድ ከነዓን በምትባል አገር ወደአለች ወደ ሴሎ መጥተው ፤

፪፤ ወይቤልዎሙ አዘዘ እግዚአብሔር በእደ ሙሴ ከመ የሀቡነ አህጉረ ዘውስቴቶን ንነብር ወሙፋራቲሆን ለእንስሳነ ፤

እኛ የምንኖርባቸው እና ከብቶቻችን የሚሰማሩባቸውን አገሮች ይሰጡን ዘንድ እግዚአብሔር በሙሴ ቃል አዝዞልን ነበር አሏቸው ፤

፫፤ ወወሀብዎሙ ደቂቀ እስራኤል ለሌዋውያን በትእዛዘ እግዚአብሔር እላንተ አህጉረ ወሙፋራቲሆን ፤

የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለሌዋውያን ከመሰማሪያቸው ጋር እነዚያን አገሮች ሰጧቸው ፤

፬፤ ወበጽሐሙ መክፈልቶሙ ለደቂቀ ቀዓት ወኮነ ለደቂቀ አሮን ካህናት እምሕዝበ ይሁዳ ወእምሕዝበ

ስምዖን ወእምሕዝበ ብንያም መክፈልቶሙ አሥሩ ወሠላስ አህጉር ፤

ለቀዓት ልጆችም ፈንታቸው ደረሳቸው፤ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ለሆኑ ለአሮን ልጆችም ከይሁዳና ከስምዖን ከብንያምም ወገኖች ዕጣ ፈንታቸውን አሥራ ሦስት አገሮችን ሰጧቸው ፤

፭፤ ወለደቂቀ ቀዓት እለ ተርፉ እም ሕዝበ ኤፍሬም ወእምሕዝበ ዳን ወመንፈቀ ነገደ ምናሴ መክፈልቶሙ አሥሩ አህጉር ፤

ቦታ ሳያገኙ ለቀሩት ለቀዓት ልጆችም ከኤፍሬምና ከዳን ከምናሴም ነገድ እኩሌታ ፈንታቸውን አሥር አገሮች ሰጧቸው ፤

፮፤ ወለደቂቀ ጌድሶን እምነገደ ሕዝበ ይሳኮር ወእምሕዝበ አሴር ወእም ሕዝበ ንፍታሌም ወእመንፈቀ ነገደ ምናሴ በባሳን መክፈልቶሙ አሥሩ ወሠላስ አህጉር ፤

የጌድሶንም ልጆች ዕጣ ከይሳኮርና ከአሴር ፤ ከንፍታሌምና ከምናሴም ነገድ እኩሌታ ሆነ በባሳን ያሉ አገሮቻቸውም አሥራ ሦስት ናቸው ፤

፯፤ ወለደቂቀ ሜራሪ በበሕዘቢሆሙ እምነገደ ሮቤል ወእምነገደ ጋድ ወእምነገደ ዛብሎን መክፈልቶሙ አሥሩ ወክልኤ አህጉር ፤

የሜራሪ ልጆች ዕጣም በየወገናቸው ከሮቤልና ከጋድ ከዛብሎንም ልጆች አገር ሆነ ፤ እነዚህ አወጣጥተው የሰጧቸውም ፲፪ አገሮች ናቸው ፤

፰፤ ወወሀብዎሙ ደቂቀ እስራኤል አህጉረ ለሌዋውያን ወሙፋራቲሆሙ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ለሙሴ መክፈልቶሙ የሀብዎሙ ፤

የእስራኤልም ልጆች ለሌዋውያን ዕድል ፈንታቸውን ይሰጧቸው ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው የሚኖሩባቸውን አገሮች ከመሰማሪያቸው ጋር ሰጧቸው ፤

፱፤ ወወሀቡ ነገደ ደቂቀ ይሁዳ ወነገደ ደቂቀ ስምዖን እላንተ አህጉረ ፤

ዩይሁዳና የስምዖን ልጆች ነገድ እነዚህን አገሮች ሰጧቸው ፤

፲፤ ወተሰምያ ለደቂቀ አሮን እም ሕዘበ ቀዓት ወእምደቂቀ ሌዊ እስመ ሎሙ ኮና መክፈልቶሙ ፤

እነዚህም ለአሮን ልጆች ዕድል ፈንታቸው ሁነዋልና ከሌዊ ልጆች ከሚሆኑ ከቀዓት ወገን ተለይተው የአሮን ልጆች ዕጣ ተባሉ ፤

፲፩፤ ወወሀብዎሙ ምድረ ቀርታር ቦቅ ደብረ አህጉረ ኤናቅ እንተ ይእቲ

ኬብሮን ዘደብረ ይሁዳ ወሙፋራቲሃኒ ዘአውዳ ፣

የኤናቅ አገሮች ተራራ የምትሆን ቀርታርቦቅ የምትባል አገርን ሰጣቸው ፣ ይህችውም በዙሪያዋ ካለ ከአውራጃዋ ጋራ በይሁዳ ዕጣ ያለች ኬብሮን ናት ፤

፲፪፡ ወአሐቃላተ ሀገር ወአዕፃዳቲሃ ወወሀቦ ኢያሱ ለካሌብ ወልደ ዮፎኒ ደወሎ ፣

የሀገሪቱንም አውራጃዎች ከመሰማሪያዋ ጋር ኢያሱ ለዮፎኒ ልጅ ለካሌብ ዕድል ፈንታ አድርጎ ሰጠው ፤

፲፫፡ ወለደቂቀ አሮን ካህን ወሀቦሙ ሀገረ ምስካይ ለቀታሊ ኬብሮን ወሙፋራቲሃ ወሎቤና ወሙፋራቲሃ ፣

ለካህኑ ለአሮን ልጆችም ነፍስ ለገደለ ሰው መማጠኛ ሊሆን ቦታ ሰጧቸው ፣ እነዚህም ኬብሮን ከአውራጃዋ ጋር ሎቤናም ከአውራጃዋ ጋር ናቸው ፤

፲፬፡፲፭፡ ወአቴር ወሙፋራቲሃ ወኤታም ወሙፋራቲሃ ወሄሎን ወሙፋራቲሃ ወዳቤር ወሙፋራቲሃ ፣

አቴርና ኤታም ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር ሄሎንና ዳቤር ከአውራጃዎቻቸው ጋር ፤

፲፮፡ ወናሰን ወሙፋራቲሃ ወዮጣ ወሙፋራቲሃ ወቤተ ሳሚስ ወሙፋራቲሃ ተሰዑ አህጉር እምክልኤ ሕዝብ ፣

ናሶንና ዮጣ ከአውራጃቸው ጋር ቤተ ሳሚስም ከአውራጃዋ ጋር ከሁለቱ ነገድ የተሰጡ እኒህ ዘጠኙ አገሮች ናቸው ፤

፲፯፡፲፰፡ ወእምነገደ ብንያም ገባዖን ወሙፋራቲሃ ወጋማላቀ ወሙፋራቲሃ ወአናቶት ወሙፋራቲሃ ወአሊሞን ወሙፋራቲሃ አርባዕቱ አህጉር ፣

ከብንያም ነገድ የተሰጡ አገሮችም ገባዖን እና ጋማላቁ ከአውራጃቸው ጋር አናቶትና አሊሞንም ከአውራጃቸው ጋር እነዚህ አራቱ አገሮች ናቸው ፤

፲፱፡ ወኵሎን አህጉሪሆሙ ለደቂቀ አሮን ካህናት እሥሩ ወሠላስ አህጉር ወሙፋራቲሆን ከማሁ ፣

የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሚሆኑ የአሮን ልጆች አገሮች መላው አሥራ ሦስት አገሮች ናቸው ፣ አውራጃዎቻቸውም እንደዚያው ናቸው ፤

፳፡ ወለደቂቀ ቀዓት ሌዋውያን እለ ተርፉ ኮና አህጉሪሆሙ እምሕዝበ ኤፍሬም ወወሀበሙ ሀገረ ምስካይ ለቀታሊ ፣

ከሌዊ ወገን ለሚሆኑ ለቀሩት ለቀዓት ልጆችም አገሮቻቸው ከኤፍሬም ልጆች ዕጣ ሆኑ ፣ ነፍስ ለገደለ ሰው መማጠኛ የሚሆን አገርንም ሰጣቸው ፤

፳፩፥፳፪፥ ሴኬም ወሙፋራቲሃ ወቤቶሮን ወሙፋራቲሃ ጌዜር ወሙፋራቲሃ ወቄበጻይ ወሙፋራቲሃ አርባዕ አህጉር ።

ሴኬምና ቤቶሮን ከመሰማሪያቸው ጋር ጌዜርና ቄበጻይም ከአውራጃዎቻቸው ጋር እሊህ አራቱ አገሮች ናቸው ፤

፳፫፥ ፳፬፥ ወእምሕዝበ ዳን ኢሊቆቱም ወሙፋራቲሃ ወገባቶን ወሙፋራቲሃ ወኤሎን ወሙፋራቲሃ ወጌቴሬምን ወሙፋራቲሃ አርባዕ አህጉር ።

ከዳን ወገኖች ዕጣ የተሰጡትም ኢሊቆቱም እና ገባቶን ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር፣ ኤሎንና ጌቴሬምን ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር እሊህ አራት አገሮች ናቸው ፤

፳፭፥ ወእመንፈቀ ነገደ ምናሴ ጠናህ ወሙፋራቲሃ ወዴቦታ ወሙፋራቲሃ ክልኤ አህጉር ።

ከምናሴ ነገድ እኩሌታም የተሰጡ ጠናህና ዴቦታ ከመሰማሪያቸው ጋር እሊህ ሁለት አገሮች ናቸው ፤

፳፮፥ ወኵሎን አህጉር አሥሩ ወሙፋራቲሆን ዘቅሩቦን ለነገደ ደቂቀ ቀዓት እለ ተርፉ ።

ለቀሩት ለቀዓት ልጆች ነገድ አቅራቢያዎቻቸው ከሚሆኑ ከመሰማሪያዎች ጋር የተሰጡ አገሮች አሥር ናቸው ፤

፳፯፥ ወለደቂቀ ጌድሶን ሌዋውያን እመንፈቀ ነገደ ምናሴ አህጉር እለ ፈለጡ ምስካየ ለቀታሊ ጋውሎን በባሳን ወሙፋራቲሃ ወአስጣሮት በባሦር ወሙፋራቲሆን ፪ኤ አህጉር ።

የሌዊ ወገኖች ለሚሆኑ ለጌድሶን ልጆችም ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ከምናሴ ነገድ እኩሌታ ተለይተው የተሰጡ አገሮች በባሳን ያለች ጋውሎን እና በባሶር ያለች አስጣሮት ከአውራጃዎቻቸው (ከመሰማሪያዎቻቸው) ጋር እሊህ ሁለቱ ናቸው ፤

፳፰፥ ወእምነገደ አሴር መሴላ ወሙፋራቲሃ ወአቤዶን ወሙፋራቲሃ ወያቃቅ ወሙፋራቲሃ ወሮአብ ወሙፋራቲሃ ።

ከአሴር ነገድ ዕጣ የተለዩ አገሮችም መሴላና አቤዶን ከአውራጃቸው ጋር ያቃቅና ሮአብ ከአውራጃዎቻቸው ጋር እሊህ አራቱ ናቸው ፤

፳፱፥ ወእምነገደ ይሳኮር ቂስዮን ወዳቤራት ወሙፋራቲሆን ።

ከይሳኮር ነገድም ዕጣ የተለዩ አገሮች ቂስዮንና ዳቤራት ከመሰማሪያቸው ጋር ፤

፴፡ ወያሬማት ወኤንጋን ወመሩ ራቲሆን አርባዕ አህጉር ፡፡

ያሬማትና ኤንጋን ከመሰማሪ ያዎቻቸው ጋር እኒህ አራቱ አገሮች ናቸው ፡፡

፴፩፡፴፪፡ ወእምሕዝበ ንፍታሌም ሀገር ዘፈለጡ ለቀታሊ ቃዴስ በገ ሊላ ወመሩራቲሃ ወኤማት ወመሩ ራቲሃ ወቀርያቲአም ወመሩራቲሃ ሠላስ አህጉር ፡፡

ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ከንፍታሌም ዕጣ የለዩዋቸው አገሮችም በገሊላ ያለች ቃዴስ ከመሰማሪያዋ ጋር ኤማትና ቀር ያቲአም ከአውራጃቸው ጋር እሊህ ሦስቱ አገሮች ናቸው ፡፡

፴፫፡ ወኵሎን አህጉር ዘጌድሶን በበ ሕዘቢሆሙ አሥሩ ወሠላስ አህጉር ፡፡

በየወገናቸው የጌድሶን ልጆች የተቀበሏቸው አገሮች አሥራ ሦስት ናቸው ፡፡

፴፬፡ ወለነገደ ሕዝበ ሜራሪ እለ ተርፉ እምሌዋውያን እምሕዝበ ዛብሎን ኢያቅማን ወመሩራቲሃ ወቃዴስ ወመሩራቲሃ ፡፡

ከሌዋውያን ወገን ለቀሩ ለሜ ራሪ ወገኖች ከዛብሎን ዕጣ የተ ለዩ አገሮች ኢያቅማንና ቃዴስ ከመሰማሪያዎቻቸው ጋር ፡፡

፴፭፡ ወሴላ ወመሩራቲሃ ሜጌታኒ ወመሩራቲሃ አርባዕ አህጉር ፡፡

ሴላና ሜጌታኒ ከመሰማሪያ ቸው ጋር እሊህ አራቱ አገሮች ናቸው ፡፡

፴፮፡፴፯፡ ወበማዕዶተ ዮርዳኖስ ዘመ ንገለ ኢያሪኮ እምሕዝበ ሮቤል ሀገረ ምስካይ ለቀታሊ ባሶር በገዳም ወመ ሩራቲሃ ወያዜር ወመሩራቲሃ ወቄ ዴሞት ወመሩራቲሃ ወሜፌአት ወመሩራቲሃ አርባዕ አህጉር ፡፡

በኢያሪኮ አንፃር ባለች በዮር ዳኖስ ማዶም ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ከሮቤል ዕጣ የተለዩ አገሮች በምድረ በዳ ያለች ባሶርና ያዜር ከመሰማ ሪያዎቻቸው ጋር ፡፡ ቄዴሞትና ሜፌአትም ከመሰማሪያዎቻ ቸው ጋር እሊህ አራቱ ናቸው ፡፡

፴፰፡፴፱፡ ወእምሕዝበ ጋድ ሀገረ ለምስካየ ቀታሊ ሬሞት በገለዓድ ወመሩራቲሃ ወምናኤም ወመሩራ ቲሃ ፡፡

ለነፍሰ ገዳይ መማጠኛ ሊሆኑ ከጋድ ወገኖች የተለዩ አገሮ ችም በገለዓድ ያለች ሬሞትና ምናኤም ከመሰማሪያቸው ጋር ፡፡

ወሐሴቦን ወመሩራቲሃ ወኢያዜር ወመሩራቲሃ አርባዕ አህጉር ፡፡

ሐሴቦንና ኢያዜር ከአውራጃ ቸው ጋር እሊህ አራቱ ናቸው ፡፡

፵፡ ወኵሉ አህጉሪሆሙ ለእለ ተርፉ እምነገደ ሌዊ ለደቂቀ ሜራሪ በበነገዶሙ ወከነ ደወሎሙ አሥር ወክልኤ አህጉር ፣

ከሌዊ ነገድ ለቀሩት ለሜራሪ ልጆች በየነገዳቸው የደረሷቸው አገሮች ሁሉ እነዚህ ናቸው አውራጃቸውም አሥራ ሁለት ነው ፤

፵፩፡ ወኵሎን አህጉሪሆሙ ለሌዋውያን በማእከለ ደወሎሙ ለደቂቀ እስራኤል አርባዓ ወሰማኒቱ አህጉር ወሙፋራቲሆን ዘዓውዶን ለእማንቱ አህጉር ፣

በእስራኤል ልጆች አውራጃ መካከል ያሉ የሌዋውያን አገሮች ሁሉ በዙሪያቸው ካሉ መሰማሪያዎቻቸው ጋር አርባ ስምንት አገሮች ናቸው ፤

፵፪፡ ለለሀገር ወሙፋራቲሃ ዓውዳ ለሀገር ከማሁ ለኵሎን እላንቱ አህጉር ፣

ባገሩ ዙሪያ ያለ ያንዲቱም ያንዲቱም ሀገር መሰማሪያዋ እንደነዚያ (እንደሌሎቹ) አገሮች መሰማሪያ ነው ፤

፵፫፡ ወወሀቦሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ኵሎ ምድረ ዘመሐለ ለአበዊሆሙ ወተዋረስዋ ወነበሩ ውስቴታ ፣

እግዚአብሔርም ለእስራኤል ልጆች አዋርሰችኋለሁ ብሎ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን አገር ሁሉ ሰጣቸው ፣ ወረስዋትም በውስጧ ኖሩ ፤

፵፬፡ ወአዕረፎሙ እግዚአብሔር እምእለ ዓውዶሙ በከመ መሐለ ለአበዊሆሙ ፣

ለአባቶቻቸው እንደማለላቸው እግዚአብሔርም ወደ ምድረ ርስት አግብቶ በዙሪያቸው ካሉ ጠላቶቻቸው አሳረፋቸው ፤

ወአልቦ እንከ መኑሂ ዘተቃተልዎሙ እምቅድመ ገጾሙ እምኵሉ ጸሮሙ እስመ አግብኦሙ እግዚአብሔር ለኵሎሙ ጸሮሙ ውስተ እደዊሆሙ ፣

እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ሁሉ በእጃቸው ጥሎላቸዋልና ከዚያ በኋላ ከጠላቶቻቸው ወገን ማንም ማን በፊታቸው ተሰልፎ የተጣላቸው የለም ፤

፵፭፡ ወኢተርፈት አሐቲ ቃል እምኵሉ ሠናያት ዘይቤሎሙ እግዚአብሔር ለደቂቀ እስራኤል ኵሉ በጽሐሙ ፣

እግዚአብሔር ለእስራኤል ልጆች አደርግላችኋለሁ ብሎ ከነገራቸው በጎ ነገር ሁሉ ሁሉም ደረሳቸው እንጂ አንዲትም የቀረች ቃል የለችም ።